<u>ሁለተኛው የውሸት (ሐሰት) በደል በድሏል፤</u>

ቅዱስነታቸው አለመታመማቸው እየታወቀ፣ በውሸት ሰብአዊ መብታቸውን ገፍፎ ታመዋል ብሎ መዋሸቱ ታላቅ በደል ነው። *"በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር"* በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ሕግና፥ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ሚዛን ሲመዘን፣ ውሸታምም ወንጀለኛም ስለሆነ፣ የሚሰጠው ብይን ሁሉ ተአማኒነትም፣ ተቀባይነትም የለውም።[562] ሰውን እንደ ሰው ማክበር፣ ማለትም የቅዱስ ፓትርያርኩ ጉዳይ የተወሰነው፣ እርሳቸው በሰውነታችው ተጠይቀው የሆኑትን ተናግረው ሳይሆን፣ እርሳቸው ያልሆኑትን ሆኑ ተብሎ የውሸት ችግር በእርሳቸው ላይ እንዲለጠፍ ተደርጎ ነው።[563]

ይህም የውሸት በደል ፓትርያርኩ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለቅዱስ ሲኖዶሱ ሰጥተዋል በማለት የተነገረው ነው፤ ይህ ውሸት ፓትርያርኩን ኃላፊነታቸውን እንዳልተወጡ አድርጎ ከማሳየቱም በላይ፣ ቅዱስ ፓትርያኩን በመበደል ተጠያቂ ሊሆን የሚገባው ሲኖዶስ፣ የቤተ ክርስቲያንን ችግር የሚፈታ እውነተኛ ሲኖዶስ ነው ሊባል አይችልም። ስለዚህ ይህ ሲኖዶስ፣ ቤተ ክርስቲያንን የማይወክል ውሸታም በመሆኑ፥ በፓትርያርኩ ላይ ወሰንኩት ያለው ሁሉ እንደ ቅዱስ ሲኖዶስ ተቆጥሮ በውሳኔነት ሊጸድቅ አይችልም።[564] የጉዳዩን እውነተኝነት ለማጠናከር፣ እየተከናወነ ያለውን እንቅስቃሴ መመልከት ይቻላል። ለምሳሌ የአዲስ አበ

[562] ዝኒ ከማሁ
[563] ዝኒ ከማሁ
[564] ዝኒ ከማሁ



ባው ሲኖዶስ ለአንድነት ይጠቅማል በማለት ለሁለተኛው ዙር ድርድር ያቀረበው የመደራደሪያ አጀንዳ እንዲህ ይነበባል።

*"አራተኛው ፓትርያርክ አቡነ መርቆሬዎስ ሥልጣናቸውን የለቀቁት በሕመም ምክንያት በፈቃዳቸው መሆኑን እንዲናገሩ፤ ኢትዮጵያ ገብተው ስማቸው በቅዳሴ ላይ እየተጠራ እንዲቀደስ፤ ደመወዛቸው እየተከፈላቸው በአንድ ደብር ተወስነው የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ ጠባቂ እንዲሆኑ፣ ውሳኔ መስጠት የሚችሉት ግን አቡነ ጳውሎስ እንዲሆኑ፤ በሰሜን አሜሪካ የተሾሙ ጳጳሳትም አገር ቤት ገብተው መሥራት ከፈለጉ እንዲችሉና እዚህ/ በአሜሪካ/ ሁነው መሥራት ከፈለጉ፣ በአዲስ አበባው ሲኖዶስ ሥር ሁነው እንዲሠሩ" ይላል።*[565]

በአባ ሰላማ ድኅረ ገጽ ደግሞ ሕጋዊው ሲኖዶስ እንደ ሕገ ወጥነት የተቆጠረበትን ይቅርታ እንዲጠይቅበት የቀርበለት ቅድመ ሁኔታ እንዲህ ሰፍሯል " *የተሰደደ ሰው በውጭ አገር ሌላ ሲኖዶስ አቋቁሞ ሌሎች ጳጳሳትን መሾም ትክክል አይደለም። ይህን እንደ ስህተት መቀበል አለባቸው፤"* የሚል ነው።[566]" እንደ ስህተት የተቆጠረበት በውጭ አገር ሁኖ ጳጳስ መሾም አግባብ አይደለም የሚለው ከሆነ፣ ይህን ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን አንጻር ስንመለከተው ምን ይመስላል? የሚለው የመጀመሪያው ጥያቄ የሲኖዶስን ምንነት ማወቅ ነው።

<u>ሲኖዶስ ማለት</u>፤ ከሁለት በላይ ጳጳሳት ለተገኙበት ስብሰባ ወይም

[565] *ከኢትዮጵያን ሪቪው ድኅረ ገጽ የተገኘ፤*
[566] *ከአባ ሰላማ ድኅረ ገጽ የገኘ፤*

ጉባኤ የተሰጠ ስም ነው። በሐዋርያት ቀኖና ከሁለት በላይ ጳጳሳት የጵጵስና ሥልጣን የመስጠት መብት ያላቸው ሲሆን፣ እነርሱ የሾሙት ጳጳስ ሥልጣንም በኦርቶዶክሳዊ ቆኖና ተቀባይነት አለው። እውነቱ ይህ ከሆነ፣ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ አምስት ሊቃነ ጳጳሳት ያሉበት፣ በፓትርያርክ የሚመራ ቅዱስ ሲኖዶስ ጳጳስ ስለሾመ ስህተት ነው፣ ማለት በትውፊታዊው ቀኖና መሠረት ነገሩን ስናየው፣ ቀኖናን ካለማወቅ የመጣ ችግር፥ ወይም ሆን ተብሎ እውነቱን በሐሰት ለመለወጥ የሚናገሩት ብልጥነት ነው። ስለ ሆነም የአዲስ አበባው ሲኖዶስ፣ ቅዱስ ሲኖዶስ ምን ማለት እንደሆነ አለማወቁን የሚያመለክት ስህተት እንጂ፥ ሕጋዊውን ቅዱስ ሲኖዶስ ይቅርታ የሚያስጠይቅ ጉዳይ የለውም።

<u>ሦስተኛው፣ ሥልጣናቸውን የለቀቁት ታምመው ነው፤</u> የሚለው ስህተት ነው። ለዚህም፣ የአዲስ አበባው ሕገ ወጥ ሲኖዶስ ይህን ያለበትን የጊዜ ገደብ መመልከት ይጠቅማል። የዚህን ሐሳብ ስህተት የሚያረጋግጠው ፓትርያርኩ ታመው መሥራት አልችልም ብለው ቦታቸውን የለቀቁት መቸና የት ነው? የሚለው ጥያቄ ሲመለስ ብቻ ነው።

ፓትርያርኩ ታመው ሥልጣናቸውን ለቀቁ የተባለው ወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት ሁኖ አገር በተቆጣጣረበት ጊዜ ነው። ዘመኑ ይኸውና ከሀያ ዓመት በላይ ሆነ። ያን ጊዜ የታመመ ሰው እስከ አሁን ድረስ ያውም በስደት እንዴት ጤናማ ሁኖ ኖረ? ነው ጥያቄው። ይህንም የነሱን *"ሥልጣን የለቀቁት በጤና ምክንያት ነው"* የሚለውን ሐሳብ እንቀበል ብንል እንኳ፣ ከሃያ ዓመት በኋላ ምክንያት አድርጎ ማቅረቡ፣ ከጤናማ አእምሮ የመነጨ ጤናማ ሐሳብ አይደለም። በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ብንመዝነውም ሚዛን



ሊደፋ አይችልም። ስለዚህ ይህን የተሳሳተ ሐሳብ፣ ቀጥሎ በቀረበው መልኩ ማስቀመጥ እንችላለን።

<u>አንደኛ፣</u> የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሕጋዊ የፓትርያርክነት ሥልጣን በአ ዲስ አበባ በሚገኘው ሲኖዶስም ሊካድ የማይችል ሁኖ መቅ ረቡ እውነት ነው።

<u>ሁለተኛ፣</u> ለድርድር በቀረቡ ጊዜ ቅዱስ ፓርያርኩ የቤተ ክርስቲ ያን የበላይ ጠባቂ ይሁኑ ማለታቸው፣ አባ ጳውሎስ የአስተዳደር ሥራ የሚሠሩ የሲቢል ሥራ አስኪያጅ እንጂ በክህነት ደረጃ ክህነታቸው አይሠራም ማለት ነው፤ ምክንያት በአንድ ጊዜ በአ ንድ መንበር ሁለት ፓትርያርኮች ሊቀመጡ አይችሉምና። ይህም እነሱው ካሉት በመነሣት ነው።

የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ፣ የሚለው አባባል በኦቶሰፋሎስ ቤተ ክርስቲያን መርሕ መሠረት፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ ፓትርያርክ የሚባለው የአስተዳደሩን ሥራ የሚሠራው ሳይሆን፥ የመንፈሳ ዊው የበላይ ጠባቂ የሆነው አባት ነው ፓትርያርክ የሚባለው።[567] ይህም አሁን ባለንበት ዘመን የኦርቶዶክሱ ዓለም *"ፓትርያርክ"* የመንፈሳዊው ሥልጣን የበላይ የሆነው የአስተዳደር ሥልጣን የለውም። ያ ማለት እኛን ጨምሮ የጥንት ቤተ ክርስቲያን አሠራር እንደዚሁ ነበር።

[567] *John Meyendorff ,Vision* of Unity. P. 101

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት የኖረችው፣ የግብፁ ፓትርያርክ የአስተዳደሩን ሥራ እየሠራ አልነበረም፤ ሁኖም ግን የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ነበር። እርሱ የሾመውን ሊቀ ጳጳስ ወይም ኤጲስቆጶሱን ወክሎ ነው ማለት ነው፤ ስለዚህ ስደተኛው ሲኖዶስ ይህን ሁሉ ለመደራደሪያ ሐሳብ ማቅረብ አለበት። በአጠቃላይ ይህ ሁሉ በቀኖናዊ መልክ ተይዞ በመልስ ደረጃ አጀንዳ በመሆን መሟገቻ ሐሳብ ሊሆን የሚች ነው።

የአዲስ አበባውን ሲኖዶስ ሌላም ቀኖናዊ ስህተት አለበት፣ ይኸውም በቅዱስ ፓትርያርኩ ላይ የተሳሳተው ሳይበቃ፣ በሕይወት ባሉት ሕጋዊ ፓትርያርክ ላይ ምንም ዓይነት ውሳኔ ሳይሰጥ፥ በሕገ ወጥ መንገድ አምስተኛ ፓትርያርክ መምረጡ፥ በሕገ ቤተ ክርቲያን ላይ በደል ሠርቷል። [568] የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ለዚህ ክስ ቀኖናዊ መልስ የለውም። በድርድሩ ወቅት፣ በሕመም ምክንያት መሥራት ስላልቻሉ፣ በምትካቸው አባት ለመተካት የተወሰነው በምልዓተ ጉባኤ ስለ ሆነ፣ ቀኖና ይፈቅዳል የሚል መሟገቻ አቅርበዋል።[569]

ከሁለት በላይ ጳጳሳት ከተሰበሰቡ ቤተ ክርስቲያንን የሚወክል ቀኖናዊ ሲኖዶስ በመሆኑ በሱ ላይ መስማማት ቢቻልም፣ የጳጳሳት መሰባሰብ ብቻውን ግን ሲኖዶሳዊ ምልዓተ ጉባኤ ሊያሰኝ አይችልም። ምክንያቱም ስብሰባው የተካሄደው የቤተ ክርስቲያንን ሕግ ተከትሎ ካልሆነ፥ ጉባኤው ቤተ ክርስቲያንን የሚወክል

---

[568] *ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ አምስት ቁጥር 75*
[569] *ከሰላም ኮሚቴው የተገኘ መረጃ*



ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ለመሟገቻ የቀረበው ሐሳብ ቀኖናዊ ሚዛን ስለማይደፋ ለአዲስ አበባው ሲኖዶስ ሕጋዊነት በሁለት መንገድ ቀኖናዊ ድጋፍ ያሳጣዋል።

<u>በመጀመሪያ፤</u> የአዲስ አበባው ሕገ ወጥ ሲኖዶስ፥ ሕጋዊውን ሲኖዶስ ሲያፈርስ፣ በምልዓተ ጉባኤ ሳይሆን፤ በተወሰኑ የወያኔ ኢሕአዴግ ደጋፊ ጳጳሰት በስውር በመሆኑ፤ [570] ያው ሕገ ወጡ ሲኖዶስ ዐቃቤ መንበር ብሎ የሾማቸው ሰውም የተመረጡት[571] በምልዓተ ጉባኤ አይደለም፤ ስለ ሆነም በሕገ ወጡ ሲኖዶስ በተመረጡት ዐቃቤ መንበር አማካይነት ምልዓተ ጉባኤው ተጠራ። ይህ ማለት ያለ ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ በሕገ ወጥ መንገድ በመንግሥት ፈቃድ በተቀመጡት ዐቃቤ መንበር የተመራው ይህ ጉባኤም፥ እንደ እውነተኛ ጉባኤ ተቆጥሮ ቤተ ክርስቲያንን የመወከል ቀኖናዊ መብት አልነበረውም ማለት ነው።

በዚህም ምክንያት በስውር ተደራጅቶ የነበረው ቡድን የሲኖዶሱን አባላት በሥርዓት መጥራት አቅቶት ከሲኖዶስ ውጭ በመንግሥት አስተባባሪነት በተመደቡ ሽምጋዮች አማላጅነት ነበር ጥሪውንም ያደረገው፤ በዚህ ሁሉ ምክንያት ሲኖዶሱ ሕገ ቀኖናውን መጣሱን ካላመነ፥ አሁንም ከዚህ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚያስጠብቅ ቁም ነገር ይገኝበታል ብሎ ማሰብ ይከብዳል።[572] ምክንያቱም ያለፈውን ስህተት መቀበል ካልተቻለና ስሕተቱ ካልታረመ፣ ያው ስህተት ላለመደገሙ ምን አስተማማኝ ነገር ይገኛል?

---

[570] *የተከደነ የማይገለጥ የለም።*
[571] *ዝኒ ከማሁ*
[572] *ዝኒ ከማሁ*

በአንጻሩ ስደተኛው ሲኖዶስ ከሁለት በላይ ጳጳሳት ሲኖዶሳዊ ቀኖናን ያሟላሉ የሚለውን የቤተ ክርቲያን ቀኖና ከማሟላቱም በላይ የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ምንም ውሳኔ ያልሰጠባቸው ሕጋዊውን ፓትርያርክ በቤተ ክርስቲያን መሪነት ተቀብሎ በእርሳቸው ስለሚመራ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን የመምራት ቀኖናዊ መብት አለው፤[573] ምክንያቱም ቀኖና ያልሻራቸውን ፓትርያርክ አባት ማድረግ ዓለም አቀፉ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ግድ ይላልና።

ይህ አሳሳቢ ጉዳይ ከቤተ ክርስቲያን ቀኖና አንጻር የሚታይ ከሆነ፣ ቀኖናን የማስጠበቁ ሂደት እስከ ምን ድረስ መሄድ እንደሚገባ ማሳወቅ ያስፈልጋል። በአንድ መንበር፥ በአንድ ጊዜ፥ ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ሁለት አባት በሥልጣንና በማዕረግ ለማኖር እንኳን መንፈሳዊው የቤተ ክርስቲያን ሕግ፣ ሥጋዊው የዓለም ሕግም እንኳ ቢሆን አይፈቅድም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያንድነትና የሰላም ጉባኤ፥ ፈተና ውስጥ እንዳይገባ መጠንቀቅ ያለበት ከዚህ ላይ ነው።

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቆንስጣንጢን የሰላም ጉባኤ ፈተና ውስጥ የገባው በዚህ ጊዜ ነበር፤ ሁለቱ ፖፖች እውነተኛው እኔ ነኝ ካሉ፣ ማን ይልቀቅ በማለት ከመቸገር ይልቅ፥ ሌላ መምረጥ ይሻላል፣ በማለት ሦስተኛ ፖፕ ለመምረጥ ያሳለፉት ውሳኔ አሁን ድረስ የካቶሊክ ቤት ክርስቲያን እንድታፍር ያደረጋት ታሪክ ተመዝግቧል።[574] ለዚህ ችግር በዚህ የታሪክ ሂደት ያለፈችውን የአርማንያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በምሳሌነት ማየት፥ ምን አልባት ለጊዜያዊ መፍትሄነት እንደ አማራጭ ማድረግ ይቻል ይሆናል።[575]

የአርማንያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አንዱ በአንዱ ቅባሎት ያገኘ ሦስት ፓትርያርኮች አሏት፣ ይህ ሲደረግ ግን ከላይ እንደ ተጠቀሰው በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ላይ ተመሥርቶ ሕጋዊ ጥናት በማጥናት ነው እንጂ፣ በተራ አሉባልታ የሚነዱ፣ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ቤተ ክርስቲያንን ተጠግተው የሚጎዱ፤ አንዳንድ ራስ ወዳድ ግለሰቦችን ሐሳብ ይዞ አይደለም። ይህን መሠረታዊ ጥናት ለማጥናትና ለቤተ ክርስቲያኒቱ ችግር መሠረታዊ መፍትሔ ለማምጣት ግን ከፍፍሉ ከፍተኛ እንቅፋት ሁኖ ይታያል።

ሁለተኛው ቡድን በሦስተኝነት ተገልሎ ከሁሉም አይደለሁም እያለ ያስቸገረው ቡድን ችግሩ እንድዳይፈታ አንድነቱ እንዳይመጣ የጉረሮ አጥንት ሁኖ ቆይቷል። ይኸው ቡድን *"የፓትርያርክ ሥልጣን ለእኔ ይገባል፤"* የሚል አቋም የያዘ ነው በመባል የሚታማው ቡድን ነው።[576] ይኸ ቡድን፥ ራሱን ከሁሉም በማግለል ያለምንም ቀኖናዊና ትውፊታዊ ድጋፍ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ የሥልጣን ባለቤቷና ተጠሪዋ እኔ ነኝ፣ የሚል አቋም ያለውና፥ ለቤተ ክርስቲያን ሠርተናል የሚሉ ከፍሎች ያሉበት ቡድን ነው። በብዙዎች ደብረ ሊባኖስ መራሹ ቡድን በመባል ይታወቃል።[577]

[573] *ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት ቍጥር ሰደሳ አራት*
[574] Hans kung, Christianity Essence, History,and the Future.pp. 464-470

[575] Armenian Church, Historical Studies, Matter Doctrine and Adminstration, pp. 231-300.
[576] *ለይኩን ብርሃኑ ዶክተር "ለምንት አንገለጉ ለሕዛብ።" ገጽ 135-139*
[577] *ዝኒ ከማሁ።*

ይህ ቡድን ገለልተኛ ነኝ ከሁሉም አይደለሁም፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ እውነተኛ አባት የላትም። እውነተኞች አባቶች ሙተዋል፣ ወይም አልተወለዱም፣ እነሱን እስከታገኙ ድረስ ያለ ክህነት ኑሩ የሚል ኑዛዜ አለን፤[578] በማለት ያለምንም ትውፊታዊ ቀኖና ድጋፍ የሚን ቀሳቀስ አካል ነው። ቡድኑ እንደ አስፈላጊነቱ የወያኔ ኢሕአደግን ቋንቋ እያራገበ የሚገኝ ቡድን ነው።

የስደቱ መነሻ የወያኔ ኢሕአደግ አምባ ገነናዊ ጣልቃ ገብነት ነው እንዳይባልና የአባቶች በግፍ መሰደድ እንዳይታወቅ፤"ሲኖዶስ አይሰደደም፥ ፓትርያርኩ ከዚያው ከሀገራቸው ላይ በወያኔ መገ ደል ነበረባቸው፤" ይላል። በአንጻሩ ስደተኛው እንዲቀበለው፤ ደግሞ፣ አባ ጳውሎስን አንቀበልም፤ የአዲስ አበባውን ሲኖዶስ ግን እንቀበላለን፣ ነገር ግን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን መመራት ያለ ባት በምእመናን ነው፤ በማለት እያምታታ ችግር ፈጣሪ ክፍል ሁኖ ተገኝቷል።[579]

በስደተኛ ስም ያሉትም ቢሆን፣ አሁን አሁን ሲታዩ፣ በሦስተኛ ቡድን ካሉት ቡድኖች የተለየ ሐሳብ የላቸውም ወደሚያስብላ ቸው መንገድ እየተጓዙ ይመስላል።[580] በሁሉም በኩል በመሪነት ደረጃ ያሉት ግለሰቦች በሠለጠኑበትና በዓለም በተማሩት ትምህ ርት፥ ፖለቲካውንም ሆነ ሌላውን የፍልስፍና ትምህርት ለማራ መድ ሲያቅታቸው በቤተ ክርስቲያን ገብተው አንድ ጊዜ ዓለም አቀፍ የክርስቲያን ጉባኤ፣ አንድ ጊዜ የተባበሩት አብያተ ክርስ

*[578] ዶክተር አክሊሉ ሐብቴ የብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ፍትሐት ያደረጉት ንግግር።*
[579] የማኅበረ ቤተ ክርስቲያን.
[580] ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴና ማኅበረ ቤተ ክርስቲያን የተባሉት ቡድኖች፣ ድጋፍ ሰጭ በአቡነ መልከ ጼዴቅ፥ ማኅበረ ቤተ ክርስቲያን፥ በአቡነ ይስሐቅ መደገፋቸው ነው ልዩነቱ።



ቲያናት ኅብረት፤ ሌሎቹ ደግሞ የሲኖዶስ ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ፥ ሌሎቹም አባቶችን ደጋፊ[581]እያሉ፣ ሲያሻቸው አማካሪ፣ ሲፈል ጋቸውም ፕሬዚደንት እየሆኑ፣ ፖለቲካ ሲሏቸው ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ ክርስቲያን ሲሏቸውም፣ የአገር ጉዳይ እያሉ፣ ሕዝቡንም፥ አባቶችንም ግራ እያጋቡ፣ ያሉ ቡድኖች ናቸው። ሁኔታቸው ሲታይ ግን የቤተ ክርስቲያናችን ችግር፣ በእነዚህ ዓይነት ሰዎች ይቆሰላል እንጂ አይፈዎስም።

የሚገርመው ሁለቱም ቡድኖች አንዱ ሌላውን ይወነጅላል።[582] የነዚህ ቡድኖች የከፋው ነገር ትክክለኛው ዓላማቸው በሕዝብ አለመታወቁና፣ ዓላማቸው ወያኔ ሁኖ ሳለ በምላሳቸው ብዙ እየ ተናገሩ በተወሰነ ደረጃ ተቃዋሚ መስለው መታየታቸው ነው።[583] እነዚህ ቡድኖች ተለዋዋጭነታቸውም አደገኛ ያደርጋቸዋል። በዚህ ባሕርያቸው እነዚሁ ቡድኖች በሐሳብ የማይስማሙ የሚ መስሉ ነገር ግን በሚሠሩት ሥራ አንድ ዓይነት የጥፋት ውጤት የሚታይባቸው ናቸው።

ከውጭ ለሚመለከታቸው የተለያየ ዓላማ ያላቸው ይመስላሉ። አንድ ጊዜማ ድጋፍ ሰጭ አባላትና ገለልተኛ በአንድ ላይ ተሰብ ስበው ለቤተ ክርስቲያን መመሪያ ለማውጣት ተስማምተው እንደ ነበር ይታወሳል። የሁለቱ ዓላማ አንድ መሆኑን የሚጠቁሙበት

[581] ማኅበረ ቤተ ክርስቲያን ለምዕራብ ሀገሮች ሀገረ ስብከት አስተዳደር የወጣ ደምብ ሚያዝያ 2/ 1992 በተጻፈ መሸኛ የተላከ መመሪያና መዋቅር።
[582] የድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ ታላላቅ አባቶችን ሥልጣን ለማስጠበቅ በሚል መርሕ የወጣው የድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ መመሪያና ሥልጣን ለሠላሳ ሁለተኛው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ቀርቦ በአንድ ድምጽ ብቻ የተደገፈ ባለአሥራ ሁለት አንቀጽ መመሪያ።
[583] የሁለቱንም ኮሚቴዎች ዓላማ መመልከቱ የነገሩን ትክክለኛነት ያጸድቀዋል።

ጊዜ አለ። ለምሳሌ የገለልተኛ ዋና አራማጆችና፥ የድጋፍ ሰጭ ሊቃነ መናብርት በጋራ ስብሰባ ማድረጋቸው አንዱ ሲሆን፤ የገለ ልተኛ አብያተ ክርስቲያናት መተዳደሪያ ደንብን ገልብጠው የድ ጋፍ ሰጭዎች ሲጠቀሙበት ይታያል።

በሠላሳ ሦስተኛው ጉባኤም የታየው ይኸው ነው። ልዩነቱ ድጋፍ ሰጭዎች ለሚያደርጉት ስህተት፣ በዕድሜ የሸመገሉ አባቶችን ድጋፍ የሚል ቅባት ጨምረው መታየታቸው ነው። ቢሆንም ሁለተኛውና በገለልተኝነት ያለው ቡድን ግን እርሱ የማይፈል ገውን እርቅ ሕጋዊው ሲኖዶስ እንዲያደርግለት ይጥራል፤ ለዚህም "አንድነት" ለሚለው ሂደት ድጋፍ ይሰጣል።

በዚህ አካሄዱ በአገር ወስጥ ያለው ሕገ ወጥ ቡድን ይወድቃል፣ ብሎ ስለሚያምን በአንጻሩም ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ተሰናክሎ ከወደቀለት፣ የሱን ቦታ ይዞ የድል አጥቢያ አርበኛ ሁኖ ለመቅረብ ሁኔታዎችን እያመቻቸ ይቀርባል የሚሉት ብዙዎች ናቸው። ይህ ሁሉ የችግር ጥያቄ ወጥነት ያለው ቀኖናዊ መልስ ይፈልጋል። ኦርቶዶክሳዊነት የሚጠይቀው መመዘኛ በስሙ ከመጠራት ያለፈ ተግባርን ቀኖናዊ ትውፊትን ማሟላትን ነው።

አሁን ያለው አካሄድ ግን በሁሉም መንገድ ቀኖናዊ አለመሆኑ መታወቅ አለበት፤ ቀኖናዊ ካልሆነ ደግሞ ኦርቶዶክሳዊ ነው ማለት ያዳግታል። ኦርቶዶክሳዊ የሚያሰኘው አንዱና የመጀመሪያው ትውፊታዊ ቀኖናን መጠበቅና ማስጠበቅ ሲቻል ብቻ ነውና። ለዚህ ነው የጥንት አባቶች ይህን የሚጥሰውን ሲኖዶስ ያወግዘ



ዋል፣ የሚለውን የቀኖና ማሰሪያ ያበጁት።[584]

ይህንን ሐሳብ የምናጠቃልለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ችግር ከሌላው የሚለየውና ውስብስብም የሚያ ደርገውን ሁኔታ በማመላከት ነው። ይኸውም ገለልተኛ ነኝ የሚ ለው ቡድን ትውፊታዊ የቀኖና ድጋፍ ሳይኖረው፥ ያለ ሕጋዊ ክህነት ውክልና በድፍረት ቤተ ክርስቲያን ነኝ ማለቱና፣ እንዲ ሁም ሕጋዊ ነኝ የሚለውም ክፍል፥ ሕጋዊነትን ለግል ስሜቱና ዓላማው ማዋሉ ነው ማለት እንችላለን። ይሁን እንጂ የሁለቱ ዓላማ አንድ ዓይነት ነው፤ ነገር ግን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በሕዝብ ተቀባይነት በማግኘቱ በቶሎ ለማጋለጥ ከባድ ነው።

ይህ የሕዝብ አለመጠርጠርና በሕዝብም መጠነኛ ቅባሎት ማግ ኘት ደግሞ ወደ ፊት ቤተ ክርስቲያኒቱ አደጋ ላይ መሆኗን አሁን የምናየው አካሄድ የሚያረጋግጠው ጉዳይ ነው።[585] ይኸውም በአ ንድ በኩል ቤተ ክርስቲያንን የመገንጠል አዝማሚያ ይታያል። በሌላ በኩል በእደግፋለሁ ባይነት ቤተ ክርስቲያንን ዕውቀትም፥ እምነትም፥ ለሌላቸው ጨካኞች ለማስያዝ የሚደረገው አዝማ ሚያ፣ ለቤተ ክርስቲያናችን እድገትና ሰላም ከፍተኛ ችግር ሁኖ በተግባር እየታየ ነው። ይህን ቡድናዊ ሐሳብ የሚያራመዱ ወገኖች ከጥንታዊ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ጋር ፊት ለፊት እየተ ጋጩ ይገኛሉ።

[584] ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት ቍጥር አርባ ሁለት
[585] ለምሳሌም ያህል የዲሲውን ጉባኤ መመልከት ይቻላል

ምእመናንን በማያገባቸው የክህነት አገልግሎት ውስጥ አስገብቶ ቤት ክርስቲያንን ማመስ፣ መጨረሻው የማያምር፥ የተጠላ፥ የተወገዘ ነው።[586] በቤተ ክርስቲያን ልጆችና በተለይም ትውፊትንና ቀኖናን በተረዱ ሰዎች ዘንድ፥ እነዚህ ቡድኖች ለቤተ ክርስቲያን ከመሥራት ይልቅ፣ የራሳቸውን ስሜት እያዳመጡ እንደሚሄዱ ነው የሚታመነው። ሁሉም ቡድኖች በተለይም ሕገወጥና፥ ገለልተኛ፥ በመባል የሚታወቁት ቡድኖች ቤተ ክርስቲያንን ውጦ የራስ መጠቀሚያ ለማድረግ አንዱ አንዱን በዓይነ ቁራኛ እየተ መለከተ በመሽቀዳደም ላይ ይገኛሉ።[587]

ዓላማችንና አቅዋማችንን ማድረግ ያለብን፣ በዚህ ሁሉ የሚነሣው ቀኖናዊ ጥያቄ ትክክለኛ የሆነ ቀኖናዊ መልስ ማግኘት የሚቻልበትን ጥረት ማድረግ ነው። ሂደቱም እነዚህን ሲመለከት፣ እስከ አሁን ቤተ ክርስቲያኒቱ ያከበረቻቸውን ቀኖናዊ ዕሤቶች የሚያይና ከቀኖና ጋር የሚስማማ መሆን አለበት። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነውን የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ነጻነቷን ያገኘችበትን ሂደት ማስረጃ ማድረግ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።[588] የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነጻነቷን ያገኘችው በሕጋዊ መንገድ ቀኖናን ጠብቃ መሆኑ የታመነና ታሪካዊ እውነት ነው። ያ ከሆነ አሁን ለምን ያ ሕግ በሥራ ላይ አይውልም? የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት አለበት።[589]

ሕገ ወጦቹም በሕገ ወጥ መንገድ ሥልጣን መያዛቸውን የምናገኘው ይህ መልስ ሲመለስ ነው። ማረጋገጫውም ቤተ ክርስቲያናችን የራስን መቻል ሥልጣን ያገኘችው፥ ትውፊታዊ ቀኖናን ተከትላ ሕጋዊ ጥያቄ በማቅረቧ መሆኑ ሲታወቅ ነው። ይህን ታሪካዊ እውነት በተመለከተም ከፍ ብሎ ለዚሁ በተሰጠው ቦታ ላይ መጠነኛ ገለጻ መደረጉን እናስታውሳለን።[590] ስለዚህ አካሄዳችን ቀኖናዊ እውነትን መሠረት ማድርግ አለበት። ጥያቄው የሥልጣን ክፍፍል ጉዳይ አይደለም። ጥያቄው ዓለም ዓቀፉ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተሽሯል ነው። ጥረቱ ማጠንጠን ያለበት በዚህ ዙሪያ ነው።

ለዚህ መካከለኛ ቡድንም ሆነ፥ ድጋፍ ሰጭ ነኝ እያለ ለሚያውከው ቡድን ሊቀርብለት የሚገባው ጥያቄ አንተ ምንድን ነህ? በየትኛው ቀኖና ሕግ መሠረት ነው? ለእንደናንተ ዓይነት ክፍሎች ቤተ ክርስቲያንን የመምራት ሥልጣን የተፈቀደው? በየትኛውስ ጉባኤ ነው የተወሰነው? እንዲህ ዓይነቱ መብት በተለይም በሦስተኛ ምድብ ላይ ለሚገኘው ቡድን የሚጠየቀው ጥያቄ፣ የምትቀበለው ቀኖና በየትኛው ጉባኤ የተወሰነ ነው? በቍስጥንጥንያና በኒቅያ እንዳይል፣ እነዚህ ጉባኤያት የወሰኑትን ስለ ሕጋዊ የክህነት ውክልና የሚያዝዘውን ቀኖና አይቀበልም። ይኸ ቡድን የሚቀድሰውን ቅዳሴ እንኳ እንዴት እንደሚከደው መመልከት በቂ ነው።

[586] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ አምስት ቍጥር 178

[587] መቶ አርባ አንድና ፥ መቶ አርባ ሁለትን የግርጌ ማስተወሻ ይመልከቱ።

[588] የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዐት ራስን የመቻል ታሪክ ክፍል አንድና ሁለት

[589] ዝኒ ከማሁ

[590] ዝኒ ከማሁ

እነዚህን ጉባኤያት መቀበል ማለት፣ እነርሱ ያስቀመጡትን ትው ፊቱን፥ እምነቱን፥ ሥርዓቱን፥ ጠብቆ በማስጠበቅ፥ ጸንቶ መኖር ማለት ነው።[591]

በሥርዓተ ቅዳሴያችን የምንጸልየውን ጸሎት ***"ፍትሐት ዘወልድን"*** የሚያነብ ካህን ሕጋዊ የክህነት ውክልና ወይም ከትውፊታዊ ሲኖዶስ አመራር ተለይቶ ከህነት አለኝ ብሎ መናገር እንዴት ይችላል? [592] የጸሎቱ ምንባብ በሥሉስ ቅዱስ ከማመን ጀምሮ በነቢያትና በሐዋርያት ላይ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን፣ በሰባ ሁለቱ አርድእት የነአትናቴዎስ፥ የነዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ የነቄርሎስ ምስክርነት፣ የሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ፣ የመቶ ሃምሳው፣ የሁ ለት መቶው አበው ጉባኤ የእምነት ጥበቃን እየዘረዘረ መጥቶ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ፓትርያርክና የክፍሉን ሊቀ ጳጳስ አስታውሶ፣ ከራሱ የክህነት ሥልጣን ሲደርስ ጸሎቱን ይደመድማል።[593]

ይህን የቅዳሴ ሥርዓት የሚያከናውነው ካህን የቊርባንን ሥርዓት ለመፈጸም የሚያገለግልበት ሥልጣን፣ የቤተ ክርስቲያን ሀብት ነው። ሥልጣኑንም መጠቀም ያለበት በቤተ ክርስቲያን ፈቃድ ነው። [594] ይህን የማይቀበል ካህን፣ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት የተወገዘ ነው።[595] ይህን እውነት ገለልተኛ ነን ለሚሉት

[591] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተወሕዶ የእምነት መግለጫ
[592] ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ አንድ
[593] ቀኖና እርባ ዘጠኝን የግርጌ ማስተወሻ ይመልከቱ።
[594] አንቀጽ ስድት ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ፍትሐ መንፈሳዊ ገጽ 75
[595] ዝኒ ከማሁ



ከፍሎች እንዲያውቁት በድፍረት መናገርና መመስከር ያስፈልጋል ።[596]

በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያለባትን ከባድ ችግር ለሕዝብ አለማሳወቅ ታላቅ ስሕተት ነው። ከዚህ በተጨማሪ አሁን እንደሚታየው ሕጉን የምንገለገልበት ለግል ክብር ይሰጠናል በሚል ፍላጎት ብቻ እየመሰለ መጥቷል። በሌላው ዓለም የሚኖሩ ኦርቶዶክሳውያን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የሚበልጡት ቀኖናዊ ሕጉን መጠበቅና ማክበራቸው ነው።[597]

## <u>በሦስተኛ ደረጃ የምናየው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ነው፤</u>

በዚህ ክፍል የምንመከተው በሕጋዊነቱ የቤተ ክርስቲያን የአመራር መብት የኔነውና ቤተ ክርስቲያንን እምወክለው እኔ ነኝ፤ የሚለ ውን፥ በስደት ላይ ያለውን፥ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመረውን፥ ሕጋ ዊውን ቅዱስ ሲኖዶስ ነው።[598]

ይህ ክፍል ሕጋዊ ነኝ ሲል ይህንን ቀኖና የጠየቀውን ጥያቄ በሙሉ በመርሕ ደረጃ ቀኖናዊ መልስ ስላለውና ስለሚመልስም ነው። [599] ይህ መጽሐፍም ሆነ ሌሎች ልዩ ልዩ የቀኖና ሠነዶች

[596] Adolf Von Harnack, John Owen, Sourcs of the Apostolic Canons.pp. 29-35
[597] John H Erickson, The Challenges of Our Past.pp. 73-74.
[598] ነጸብራቅ መጽሔት ልዩ እትም ርእሰ አንቀጽ

[599] የማይገለጥ የተከደነ የለም።

የሚያረጋግጡት ይህንኑ ጉዳይ ነው። ከዚህ ውጭ ማሰብ አንድም ኦርቶዶክስን መካድ ነው፤ አለበለዚያም ሕጉን አለማክበር ነው። ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ሕጋዊ ነው ሲባል ይህንን ትውፊታዊ ቀኖና ለማስከበር ሲባል ነበር። የስደቱም ምክንያት ይህንን ትውፊታዊ ቀኖና ለማክበርና ለማስከበር ነው። [600] እንዲህ ከሆነ፣ ይህ እምነት በሥራ መገለጥ በተግባርም መታየት አለበት። ለዚህም በቀኖና ጥሰት ምክንያት ከሀገር ተሰዶ በስደት ሥራውን የሚሠራውን ቅዱስ ሲኖዶስ ምንነትና ዓላማ ከዚህ ቀጠሎ በሦስተኛ ምድብ እንመለከተዋለን።

ይህ ክፍል ሕጋዊ ነኝ ሲል ከላይ ሕገ ወጥ ናቸው ያላቸውን ክፍሎች በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ሚዛን ላይ አስቀምጦ ሲመለከታቸው፣ ቤተ ክርስቲያንን ከመወከልና ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ጋር የሚጋጩ ሁነው ተገኝተዋል፤ ስለዚህም ቤተ ክርስቲያንን የመወከልም፥ የመምራትም፥ መብቱም፥ ሞራሉም የላቸውም በማለት ነው። ግን ሕጋዊ ነኝ ለማለት ሕግን ተመርኩዞ በአመክንዮ ላይ የተመሠረተ ራእይ ያለው ሥራ ካልተሠራ፣ ሕጋዊ ነኝ ማለቱ ብቻውን፣ በቀጣዩ ትውልድ ከመወቀስና ከተጠያቂነት የሚያድን አይሆንም፤ ስለ ሆነም ይህ በሕጋዊነት መንገድ ቤተ ክርስቲያንን የሚመራውና የሚወከለው ክፍል ለቤተ ክርስቲያን በቂ አመራር መስጠት ይጠበቅበታል።[601]

[600] አባ መልከ ጼዴቅ የቋዋሚ ምስክርነት
[601] ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናትን በአንድነትና በሕጋዊ መንገድ ለማስተዳደር የወጣ የውስጥ የመተዳደሪያ ደንብ



ቤተ ክርስቲያንን የሚወክለው በስደት ላይ ያለው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ነው ብለናል። ይህ ክፍል የሕጋዊነት መብት አለኝ ሲል በቂ የሕገ ቤተ ክርስቲያን መረጃዎችን በማቅረብ ነው።[602] ይህ ማለትም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተመረጠና በሕጋዊ መንገድ የተሾመ ፓትርያርክ አለው። ቀኖናን ጠብቀው ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ የኖሩ፣ የቀኖናው መመዘኛ ከሚፈቅደው በላይ ለሲኖዶሳዊ ምልዓተ ጉባኤ በቂ ቍጥር ያላቸው ሊቃነ ጳጳሳት አሉት። [603] ይህን ያሟላ ከሆነ ኦርቶዶክሳዊ ቀኖና ይፈቅድለታል። ይህንን እውነት በሦስተኛ ረድፍ ሁኖ ገለልተኛ የሆነው ቡድንም፣ እንዲሁም በፖለቲካ ድጋፍ የተቀመጠው የአዲስ አበባው ሕገወጥ ሲኖዶስም ሊያስተባብል አይችልም።[604]

<u>የስደት አጠያያቂነት</u> ከዚህ ላይ "ሲኖዶስ አይሰደድም" የሚሉ ከቀኖና ይልቅ ስም ማጥፋት የሚቀድማቸው ሰዎች ስላሉ፣ ለነዚህም እውነቱን ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። የምናነሣው ጥያቄም ሊክዱት በማይችሉት እውነት ላይ የተመሠረተ ነው። "ሲኖዶስ አይሰደ ድም" ለሚሉ ሰዎች በሐሳባቸው እንስማማ ብንል እንኳ፣ የማያስኬድ ነገር ከፊታችን ይደቀናል። ይህም ቤተ ክርስቲያን ሂዳችሁ ታስቀድሳላችሁ ወይ? ለሚለው ጥያቄ፣ መልሱ አዎ ከሆነ፣ ወደ ሁለተኛው ከባድ ጥያቄ ይወስደናል።
ቅዳሴ የሚቀድሰው ቄስ ከየት መጣ? ለሚለው ከኢትዮጵያ ከሆነ የት ሁኖ ቀደሰ? ከኢትዮጵ ውጭ፥ እንዴት ሁኖ? ተሰድዶ ወይ አስፈቅዶ? በሁሉም ቢሆን አገር ለቅቆ ነው መልሱ። የካህን ከህነት ውጭ አገር ከሠራ፣ እንግዲያውስ የከህነቱ ባለቤቶች የሆኑት

[602] የማይገለጥ የተከደነ የለም። ገጽ 55
[603] ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት ገጽ ሠላሳ ኒቅያ አርባ አራት
[604] አሁንም በሁለቱም ዘንድ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሕጋዊ ፓትርያርክ ናቸው።

ጳጳሳት የጵጵስና ሥልጣናቸው፥ በሌላ ቃሉ ሲኖዶስ የትም ቦታ ሁኖ ይሠራል እንላለን።[605]

የክርስትናን መስፋፋት ታሪካዊ ሂደት ማቅረብ ምን አልባትም አእምሯቸው ከእውነት ጋር ለተጋጨባቸው ሰዎች መልስ ይሆናል ብሎ ማሰብ ተገቢ ይመስለናል። በታሪክ ሂደት ክርስትና ሲስፋፋ ቅዱሳን ሐዋርያት፥ ወንጌል ሰባኪዎች፥ ፓትርያርኮች ሲሰደዱ፣ በስደት አገር ያመኑትን እምነት በተቀበሉት ክህነት ሲያካሂዱ ነው የኖሩት። [606] ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ሲደርስ፣ ያንን ቀኖና ማን ሻረው?

ክህነትና እምነት የተመሠረተው ከቦታ ላይ ሳይሆን ከሰው ላይ ነው የተመሠረተው፤ ይህንን ሐቅ ልብ ልንል ይገባል። ከፍል ስጥኤም ተነሥተው መላ አውሮፓን በማካለል ወንጌልን ሲያዳርሱ፣ ማንነው ሐዋርያ አይሰደደም፥ ወንጌልም ቦታ አይለቅም፤ ብሎ ያልተቀበለ?[607] ያ ባይሆንስ ኑሮ ክርስትና እንዴት ይስፋፋል ብሎ ማሰብ ይቻላል? ስለዚህ ሲኖዶስ ቦታ አይለቅም የሚለው አባባል ከእውነቱ መሥመር በእጅጉ የወጣ፣ ጭፍን አስተሳሰብ ነው።

ሲኖዶስ አይሰደድም ከሚለው የአሉባልታ ሐሳብ ይልቅ የስደተኛው ሲኖዶስ አባላት አካሄዳቸው ትክክል ነውን? የሚለው ጥያቄ ነው መቅረብ ያለበት። ይህን ጥያቄም ስንመልስ ቀኖናን መሠረት አድርገን የተሳሳቱበትን የስሕተት አካሄድ እንጂ የቆሙበትን ዓላማ

[605] Creeds/Councils and Controversies. Pp. 5-8
[606] Ibid
[607] Barnes, Athanasius and Constantius .p. 87



አንኮንነውም።[608] ምክንያቱም ቀኖና ተጣሰ ብሎ መሰደድ ትክክለኛና ቀኖናዊ ስለ ሆነ ስሕተቱ መሰደዳቸው አይደለም።[609]

በስደት ክህነት የማይሠራ ከሆነ አባ ጳወሎስና አባ ማትያስ ጵጵስናቸው ይሠራል ተብሎ ሲያገለግሉ ነበር። ያውም አባ ማትያስ ተወግዘው፥ አባ ጳውሎስም ሲኖዶስን ከደው። ይህ ሲባል ግን የእነሱ ስህተት ስለ ሆነ እኛም እንሳሳት እያልን አይደለም። የእነሱ ስህተት ድፍረት ነው። ስሕተታቸው፣ ክህደታቸው ነው። ስለ ሆነም ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለሁለቱ ቡድኖች ጥያቄ ያቀርባል።

አዲስ አበባ ለሚገኘው ሕገ ወጥ ከፍል የሚያቀርበው ጥያቄ በሹመት ስም ያስቀመጣቸውን ሰው ሕገ ወጥነት ብቻ ሳይሆን ለዚህ ሥልጣን የሚያበቃ የሞራል ብቃትን ማንሣት፤ ለዚህ ሥልጣን ይቅርና በኦርቶዶክስ ቀኖና የቤተ ክርስቲያን አባል ሊሆኑ የማይችሉ መሆናቸውን በማስረገጥ ነው።[610] ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያንን ገንጥለው፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን አላውቅም ብለው፤ ተከሰው የተፈረደባቸው ሰው በመሆናቸው ነው። እኒህን ሰው የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ አድርጎ የሾመ ከፍል ሕጋዊ ነኝ ሊል አይችልም፣ የሚል ዐቢይ ነጥብ ይዞ በመነሣት ነው።[611]
በምንም ዓይነት ይህን ተቀብሎ አብሮ መሄድ የሚታሰብ አይደለም። የተወሰነው ውሳኔ በሥራ ላይ እንዳይውል በአንድ ቀጥተኛ ቀጭን ትእዛዝ በሚፈርስባት አገር፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያን በማይከበርባት ቤተ ክርስቲያን፣ መንፈሳዊ ነጻነት በሌለባት

[608] Ibid
[609] ፍትሐ መንፈሳዊ
[610] የማይገለጥ የተከደነ የለም። ገጽ 62
[611] ዝኒ ከማሁ ገጽ 63

ምድር እንዴትስ አብሮ ለመሥራት ይቻላል? የሚቻል አይደለም።[612] የዚህ ዓይነቱ አምባ ገነናዊ ባሕርይ በስደተኛውም በኩል ቢሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተለመደ እየሆነ መጥቷልና። አካሄዱ ሊታሰብበት እንቅስቃሴውም በቀኖና ቤተ በክርስቲያን ሚዛን ሊመዘን ይገባል።

ስለ አዲስ አበባው ግን ሁለቱን መጥቀስ ይቻላል፣ በሌ መድኃኔ ዓለም ቅጽረ ግቢ የቆመው ሐውልት፣ እንዲፈርስ ሲኖዶሱ ውሳኔ አስተላለፈ፤ ግን አልፈረሰም።[613] የጠፋው ገንዘብ እንዲመረመር ተወሰነ፣ ግን አልተመረመረም።[614] አሁን ጥያቄ እናንሣ፤ እውነቱን እናስቀምጥ ካልን፣ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ነው ችግሯን በነጻነት የምታቃልለው? ለሚለው ጥያቄ፣ መልሱ አሁን ባለንበት ደረጃ ያለውን መንግሥት አስፈቅዳ ካልሆነ በቀር ምንም ነገር መሥራት አይቻልም።[615]ይህ ሁኔታ ደግሞ የፖለቲካ ነጻነት ከሌለ አይቻልም ወደሚለው ትክክለኛ መልስ ያዘነበለ ይሆናል።

ቅዱስ ሲኖዶስ በኦርቶዶክሳዊ ቀኖና መሠረት እንዳይሠራ፣ መንግ ሥት በፖለቲካ የበላይነቱ ጣልቃ ገብቶ አፍርሶ ለእርሱ የሚታዝ ሕገ ወጥ ሲኖዶስ አቁሟል። ይህም በአቶ ታምራት ላይኔ ምስክ ርነት ተረጋግጧል። ስለዚህ ሕጋዊው ክፍል፥ የውይይቱን አቅጣ ጫ ማየት ያለበት፥ መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ሕግ የተጣሰው

[612] በየዓመቱ የሚካሄደው የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ውሳኔ ለምሳሌ የሐውልቱን መፍረስ መመልከት ይቻላል።

[613] ዝኒ ከማሁ

[614] በ 1991 የተቋቋመው የምርመራ አጣሪ ኮሚቴ የተጣራው ሒሳብ ሳይወጣ መቅረቱን ሐዋርያ ጋዜጣ ቍጥር 15

[615] የተከደነ የማይገለጥ የለም ገጽ 40



በፖለቲካ ተጽዕኖ ቢሆንም፣ ይዞት የተነሣው ዓላማ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተጣሰ ብሎ ከሆነ፣ በዚሁ ዓላማ ላይ የተመሠረተ የውይይት መድርከ መክፈት ነው፤[616] ይህ የውይይት መድረክ የቤተ ክርስቲያንን መጻኢ እድልም ወሳኝነት ያለው መሆኑን፣ ጥብቅ ትኩረት ማድረግ ያስፈልገዋል። ምክንያ ቱም የፖለቲካ ነጻነት እንኳ ቢመጣ፥ ይህ ሁኔታ ካልተስተካከለና አደራውን ካልተወጣ፣ የጠራ ቀኖናዊ ዓላማ አይኖርም። ሕጋዊ ነኝ ማለቱ ብቻ ሕግ ሊሆን አይችልም። ሕጋዊ መሆን ትልቁ እድል፣ በልበ ሙሉነት መሥራት ማስቻሉ ነው።

የሕገ ወጥነት ችግር ደግሞ የተጣሰው ሕግ አላሠራ ስለሚል፥ ያለ ሕግ በመመራት ከሚያለማው ይልቅ የሚያጠፋው በልጦ መገኘቱ ነው።[617] ስለዚህ ድርድሩ በሦስት ረድፍ ያሉትን ቡድኖች አንድ የሚያደርግ፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የተከተለ መሆን ይኖርበታል። በተለይ ሕጋዊ ነኝ የሚለው ክፍል በዚህ ተመርኩዞ ካልሠራ፣ መውደቂያ ገደሉ ብዙ ነው። ምክንያቱም በሁለቱም ያሉት ክፍ ሎች የሚገፉት ይህንኑ ሕጋዊ አካል ነው። አሁን እንደምናየው ግን፥ ከሥልጣን ውጭ ሕልም በሌላቸው ፖለቲከኞች የሚደለሉ አባቶች ይህን የተረዱት አይመስልም።[618]

አንድነቱ መታየት ያለበት፣ ከግል ሥልጣንና ከዕለት ጥቅም አኳያ ሳይሆን፣ የቤተ ክርስቲያንን ህልውና የሚያስጠብቅና ዳግም በቤተ ክርስቲያን ችግር እንዳያስነሣ መሠረት የጣለ መሆን

[616] ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት ገጽ 35 ቍጥር 70

[617] ዝኒ ከማሁ

[618] ለምሳሌ ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴን መመልከት ይቻላል

ይኖርበታል።[619] ለራሳቸው ስሜት ከተስማማ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የተሟላ የሚመስላቸው ግለሰቦች የሰላሙን ሂደት ከእነሱ ስሜት ጋር ማያያዝ የለባቸም። ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ ቀደም ሲል በተገቢ መልኩ እንደ ተገለጠው የነአትናቴዎስ፣ የነዮሐንስ አፈወርቅ፣ የነቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም ስደትና መንገላታት ለቤተ ክርስቲያን ቀኖና እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።[620] የነሱ ስደት ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊና ቀኖናዊ ጥንካሬዋ ከፍተኛ ቦታ እንዳለው ከማሳየቱም በላይ፣ ቤተ ክርስቲያን በጠላቶቿ ላይ የበላይነት እንዲኖራት አድርጓታል። አንድነቷንም አጠንክሯል።

አሁን እኛ ለመረጃ የምናቀርበው ቀኖናዊ ሰነድም የእነዚያ አባቶች የስደትና የመከራ ታሪክ ውጤት ነው። ይህንን ካላስከበርን ግን የአባቶቻችንን አደራ አልተወጣንም ማለት ስለሚሆን፣ ተጠያቂነታችን ባለፈውም፥ ባሁኑም ትውልድ ይሆናል። ከዚህ ለመዳን የውይይቱ አቅጣጫ ምን መሆን እንዳለበት ስለ ውይይቱ ሂደት ጠቃሚ ነጥቦችን ቀጥሎ እንመልከት።

## 3. <u>የውይይቱ አቅጣጫ ሂደትና ጠቃሚ ነጥቦች፤</u>

የውይይቱ ሂደት መሠረታዊ ነጥብ መሆን ያለበት የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ከሚያስጠብቀው ቀኖናዊ እውነት ላይ ነው።[621] *"እውነት ነጻ ታወጣችኋለች"* ተብሎ እንደ ተጻፈ። ይህ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ከፖለቲካ የተለየ መሆኑን የምንረዳበት ዋናው

[619] *Creeds/Councils and Controversies. Pp. 5-8*
[620] *Ibid and Barnaes, Athanasius and Constanntius.pp. 94-99*
[621] *Lewis J.Patsavos, Spiritual Dimnsions of the Holy Canons. pp. 17-34*



ሐቅ ነው።[622] ስለዚህ ለዚህ የሚረዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን፣ ታሪካዊ የቀኖና ሰነዶችን፣ ማሰባሰብና የአሁን ዘመን የቤተ ክርስቲያን መመሪያ ሕጎችንም አጥንቶ እስከ አሁን ቤተ ክርስቲያን የተጓዘችበትን ታሪካዊ ጉዞ ያመዛዘነ፣ ሂደት ያስፈልጋል።[623] ይህ ተፈላጊ የጥናት ሂደት፣ ሁለት ትልልቅ ምሰሶዎችን አቁመን እንድናልፍ ያደርጋል።

<u>አንደኛው፤</u> በዓለም አቀፍ ጉባኤያት ቀኖናዎች መሠረት የተቀበልነው እምነት እንዳይናጋ መሠረት ያለው ሂደት እንድንከተል ያስችለናል።[624] እምነትን የማያስጠብቅ ውይይት፣ ከዘመኑ የፖለቲካ አታካራ የተለየ ሊሆን አይችልም። ቅዱስ ሲኖዶስ ከብሔራዊ የፖለቲካ እርቅ ያለፈ ጽኑ ዓለማ ያለው መሆኑን ከተገነዘበ፣ ከተለዋዋጭ ፖለቲከኞች ጋር ከመዋዠቅ ይጠበቃል።[625] የቤተ ክርስቲያኒቱ እምነትና ሥርዓት እንዳይናጋ ያደርጋል። ለቤተ ክርስቲያን ቀጣይነትም ተስፋ ይሰጣል።

ፖለቲካ ሊለዋወጥ ይችላል። እምነት ግን ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ መሰላል ስለ ሆነ የበለጠ ቀዋሚነት አለው። እንዲያውም ሁሉም ፖለቲከኞች በክርስትናው መርሕ መሠረት ቅዱስ ሲኖዶስን መከተል አለባቸው፤ ማትለም ፖለቲካ ይለወጣል፥ ይዋረዳል። እምነት ግን ሁልጊዜ ይኖራል፤ እናም ድርድሩ ፖለቲከኞቹ ይሁንልን ከሚሉት በላይ ነው። ምክንያቱም ይህ የእምነት ማስጠበቅ ተግባር እንጂ የፖለቲካ ማስጠበቅ ጉዳይ

[622] *Ibid*
[623] *Creeds/Councils and Controversies*
[624] *Ibid*
[625] *J.N.D. Kelly, Early Christian Creeds.pp. 62-100*

አይደለምና። ይህም በጥንት ቤተ ክርስቲያን ያለው መሠረታዊ ሕግ ነው። እኛም ያን ስንከተል ብቻ ነው የጥንት ቤተ ክርስቲያንን ትውፊታዊ ቀኖና አክብረናል፥ ተከትለናል፤ ማለት የምንችለው።[626]

<u>ሁለተኛው፤</u> ቤተ ክርስቲያን ስደት ላይ ናት ስንል፤ በመንግሥት ሕገ ወጥ ጣልቃ ገብነት ምክንያት፥ ሃይማኖቷን በነጻነት ማካሄድ አለመቻሏን መናገራችን ነው።[627] ስለዚህ አሁን ሂደቱ፥ የእምነትን ነጻነት የማስጠበቅ ኃላፊነትና ግዴታ መሆኑን፤ ያላመዛዘነ ከሆነ፤ የወያኔን መንግሥት ደግፈው ከሚሠሩት ከአዲስ አበባዎቹ የተለየ ጉዳይ ሊሆን አይችልም።[628] በጥንታዊ ቀኖናዎች እንደ ተረዳነው የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ሥራው ሃይማኖትን ጠብቆ ማስጠበቅ ነው።

ይህም የሚሆነው ቀኖናዊ የሲኖዶስ አባላት ሲሟሉ ነው፤ ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያን የሥልጣን ምንጭ እንደ መሆኑ መጠን፥ በሥራ የሚታይ መሆን ይኖርበታል። የኢኮኖሚ ስደተኛ ይመስል የዕለት ከዕለት ኑሮን ብቻ የሚመራ ከሆነ ግን፤ ቤተ ክርስቲያንን ከማሰደብ ውጭ አንዳች የሚሰጠው ጥቅም የለም።[629] ስለዚህ የውይይቱ አቅጣጫና ሂደት ትውፊታዊ ቀኖናን፤ ሕጋዊ የክህነት ውክልናን፤ ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖትን አንጥሮ የሚያወጣ መሆን አለበት። ለምሳሌ በዚህ መጽሐፍ በተለያዩ ርእሶች መነሻነት እንደ ተገለጸው፤ የሐዋርያትን ቀኖና፤ የሦስቱን ዓለም ዐቀፍ ጉባኤያት

---

*[626] Ibid*
*[627] Eastern Christianity and Politics in the Twentieth Century, Edited by Pedro Ramet, Please see the Introduction*
*[628] Ibid*
*[629] Ibid*



ቀኖናዎችንና የቀኖና ምንጮችን ለመረጃነት በዚህ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል።[630]

ቅዱሳት መጻሕፍትን፥ ሲኖዶስ፥ ትእዛዝ፥ ግጽው፥ አብጥሊስ፥ ሥርዓተ ጽዮን፥ ጦማረ ጴጥሮስ፥ መጽሐፈ ኪዳን፥ ዲድስቅልያ፥ መጽሐፈ ቀሌምንጦስ፥ በጠቅላላው የጥንት ቤተ ክርስቲያን የመመሪያ ሕግና ደንብ እንደሚያዝዘው እየሠራን ነውን? ለሚለው ጥያቄ መልስ ካላገኘን፤[631] የምንሠራው ሥራ፤ የምንቃወማቸው ከሚሠሩት የተለየ ነው ማለት አይቻልም። ስለ ሆነም እየሠራን ያለነው ቀኖና እንደሚያዝዘው ነውን? የሚለው መጠይቅ፤ ሊመለስ ይገባል።

ዛሬ ባለንበት ደረጃ የሥልጣን አሰጣጥ ደረጃና መብት፤ ምን እንደ ሆነ ማወቅ የሚቻል አይደለም። የጥንቶቹ አባቶች የተጠቀሙበት መመሪያ እንዲህ ይላል፤ *"ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን፤ ኪዳንና ሲኖዶስ ዲድስቅልያና የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ያልተማረ፤ ወደ ሕይወት መንገድ የሚያደርሱ ሕጎቹንም ያላወቀ፤ ያልተቀበለ፤ ከሆነ ለአገልግሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን አይግባ"።*[632]

ይህ ሐሳብ የሚያመለክተው፤ ዕውቀትን፤ እምነትን፤ ሥርዓትንና ሕግን ያልተከተለና ያላከበረ አገልጋይ፤ በዚህ አገልገሎት ክልል ውስጥ መታቀፍ እንደማይችል ነው። ከላይ የጠቀስነው የቅዳሴ

---

*[630] Ibid*
*[631] ሐሳቡ በመጽሐፈ ዲድስቅልያ በብዛት የተዘገበ ሲሆን በተለይም ክፍል ሦስት ከገጽ 16-ክፍል አራት ገጽ 29 ይዘረዝራል*
*[632] መጽሐፈ ቅዳሴ*

ጸሎታችንን ብንመለከት በስሕተት ላይ መሆን አለመሆናችንን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ሕጋዊ የሚያሰኘንም ይህንን ሥርዓት መጠበቃችን ነው።[633] ከበፊቶቹ የቤተ ክርስቲያን ጠበቆች ጋር የሚያመሳስለንም ይህ ነው፤ ሐዋርያዊ ትውፊትን ለመቀበላችንና የተቀበልነውንም ያለምንም ጊዜያዊ ጥቅም የምናስጠብቅ መሆና ችንን የሚያረጋግጥልን፥ ይኸው በእውነት ላይ መቆማችን ነው።[634]

እነዚህ እሳቤዎች ከድርድሩ ውስጥ መግባት አለባቸው። ስንደራ ደር እኛንም ትዝብት ላይ የሚጥል ሥራ መሥራት የለብንም። ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን እናስጠብቃለን፣ ለተበደሉ ቁመናል፣ የም ንል ከሆነ፤ ቀኖናውን መመርመር አለብን። በዚያ ላይ የቆምን መሆኑን ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል።[635] ለመሆኑ ቀኖናው ምን ይላል? ቀኖና ማለት፣ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ነው ብለናል። ይህም በቤ ተክርስቲያን ትልቁ የሕግ ምንጭ ነው።[636]

## 4. ለሕዝብ መገለጥ ያለባቸው ሁኔታዎች፤

ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ አነጋገር ብዙ ዓይነት ብሔረ ሰቦችን ያሰባ ሰበች በመሆኗ፣ የምታደርገውን ሥራ ሁሉ፣ ማንንም በማይጎዳ መልኩ፥ ሁሉም ሕዝብ እንዲያውቀው ማድረግ ያስፈልጋታል።

[633] *መጽሐፈ ቅዳሴ ፍትሐት ዘወልድ*
[634] *መጽሐፈ ዲዲስቅልያ ክፍል ሁለት ገጽ 16*
[635] *ዝኒ ከማሁ ገጽ 19*

[636] *ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ አራትና አምስትን ይመልከቱ ።*



የምትሠራው ጉዳይ እውነት እስከ ሆነ ድረስ፣ ሕዝብ እንዲያው ቀው ማድረግ ቢያንስ ለሁለት ዐበይት ምክንያቶች ይጠቅማል፤

<u>የመጀመሪያው፤</u> ቤተ ክርስቲያን የያዘችው እውነት አስቀድሞ ከታወቀ፣ ሕዝበ ክርስቲያኑ ግራ ከመጋባት ይድናል። ስለ ቤተ ክርስቲያኑ በቂ ዕውቀት ያገኛል። በቤተ ክርስቲያኒቱም ላይ የባ ለቤትነት ስሜት ይኖረዋል፤ የከፉ ሰዎችን የመለያየት ዓላማም ማስቆም ይችላል። ይህ ደግሞ፣ ቤተ ክርስቲያን የቆመችበት ዋና ዓላማዋ ነው። የጥያቄው መልስ ቁጣ ከሆነ ግን፣ ያው ሰዎቹ እንደ ሚሉት ለእንጀራ ብቻ ተሰደናል ማለት ነው።

<u>ሁለተኛው፤</u> የዘመኑ የመገናኛ ብዙኃን ፍጥነት እጅግ የተራቀቀበት ጊዜ ስለ ሆነ፣ የታሰበው ሳይከናወን ሾልኮ ከወጣ ለብዙዎች የፖለ ቲካ መጠቀሚያ ስለሚሆን ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።[637] ባለፈው ሁለት ጊዜ ሁሉ የነበረው የድርድር ሙከራ ከሆቴል ሾርሾር ያለፈ ነገር ፈይዷል ማለት አልተቻለም ነበር። ጥንቃቄ የጎደለው አካሄድ መሆኑ በብዙዎች ተስተውሎ ነበር። ብዙ ሰዎች ንም አስደንግጦ ነበር።[638] ያ ሊሆን የቻለው ከስደት ያለፈ የሥራ ዕቅድ ወጥቶ ዓላማ መር ጉዞ ስላልነበረ ነው።

ለምሳሌ የመወያያ ነጥቡ ቅደመ ሁኔታ፣ ውይይቱ ሊካሄድ የሚች ለው ስህተታቸውን ማመን ብቻ አይደለም። ከዚያ ያለፈ ቤተ ክርስቲያን አገር ቤት ባሉት ሰዎቿ ምን በደል እየተፈጸመባቸው መሆኑን ተጨባጭ ማስረጃዎችንም ማቅረብ ቢቻል፤ ሕገ ወጥ

[637] የአዲስ አበባውን የልዑካን መግለጫ ለዋቢነት መጥቀሱ ይበቃል።

[638] ልዑካኑ ያወጡት መግለጫ አሁንም ዋቢ ነው።

ነታቸው ብቻ ሳይሆን፥ የሚሠሩት የአስተዳደር ሥራም የከፋ እንደ ሆነ አሳይቶ፣ ይህም ሊሆን የቻለው በፖለቲካው ተጽእኖ ምክንያት መሆኑን ማሳወቅ ተገቢ ነው።

የቤተ ክርስቲያን መሰደድ ዘር ለማትረፍ እግዚአብሔር ያዘጋጀው እንደ ሆነ በማስረዳት በውጭ ያለውን ኅብረተ ሰብም ማሰለፍ ይቻላል።[639] ይህ ሁሉ ጥንቃቄ የሚደረግበት ጉዳይ ነው። አሁንም እውነተኛ ነኝ የሚለው ስደተኛ ካለፈው ድንግርግር የተማረ አይመስልም። ለምሳሌ ባለፈው ሙከራ ጊዜ የተጻፉትን ደብዳቤዎች የሚያጠኑ የሕግ ሰዎችን በኮሚቴ መልክ ማቋቋም ቢቻል ኑሮ፣ ለውይይቱ አለመሳካት የግለ ሰብ ታሪክ ምክንያት ከሚሆን ይልቅ የሕገ ቤተ ክርስቲያን አመክንዮ ማቅረብ ይቻል ነበር። ኮሚቴው ያቀረበውን የመሟገቻ ሐሳብ፥ ለጉባኤ አቅርብ እንኳ ሲባል መስጠት ያልፈለገው፥ ወይ እንደ ተባለው ጨርሶ አልተዘጋጀም፥ ወይ ብቻውን ሊሠራው የፈለገው ነገር ነበረ ማለት ነው።[640]

እምነት ተጥሎባቸው የነበሩት፥ የዲሲ ገብርኤል ምእመናን፣ በቅዱስ ሲኖዶስ ሕግ ላለመመራት ያቀረቡት መቃወሚያ ነጥብ፥ ከወያኔ ጋር እየተደራደሩ ስለ ሆነ እነ አባ መልከጼዴቅን አናምናቸውም፤ ስለዚህም፣ ሲኖዶስ ያወጣውን ደንብ አንጠቀምም፤ በማለት የገለልተኛ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ሕግ ኮፒ አም

[639] የኢጲስ ቆጶሳት ሹመት መጽሔት ልዩ እትም ርእሰ አንቀጽ፤
[640] ከመጀመሪያው ድርድር በኋላ የተደረገው የአሐዮ ጉባኤ ላይ የታየው ይኸው ነበር።



ጥተው የካቴድራል መተዳደሪያ ደንብ ያደረጉት በዚሁ ምክንያት ይመስላል።[641]

ለዚህ ሁሉ የሚደረገውን እውነት አስቀድሞ ሕዝብ ካወቀው ግን መልስ ለመስጠት፣ የሲኖዶስ አባላትን ሳያስፈልግ የሰላም ኮሚቴ አባላትንም ሳያሳጣ ሕዝቡ ራሱ ይመልሳል። ውጤቱ በሕዝቡና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው ግንኙነት በመተማመን ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ያደርጋል። ሕዝቡ በአባቶቹ ይተማመናል።

ይህን አቅም የሚያዳብረውን፣ የጥንት አባቶችን ሰነዶች፣ ሥራየ ብሎ ማጥናት ያስፈልጋል።[642] ሙሉ ጊዜን በግል ሥራና በሌሎች ነገሮች ላይ እያዋሉ፣ ለስብሰባ ብቻ ሻንጣን ይዞ፣ ሸርጉድ ቢሉት መሳቂያ መሳለቂያ ከመሆን ያለፈ ፋይዳ የለውም። ከዚህ ሊያድን የሚችለው የሕግ ምሁራንን በኮሚቴ አዋቅሮ በምሁራኑ የተጠናውን ጥናት በመጽሔት መልክ ለሕዝቡ እንዲዳረስ ማድረግ፣ በዚያ ውስጥ የሕጋዊው ሲኖዶስ የሕጋዊነቱ ምንነት አቅዋምና ዓላማ እንዲታወቅ በማድረግ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።[643]

ይህ እውነት እስከሌለን ድረስ፣ ሌላውን በማውገዝ ብቻ የእኛ ሥራ ሊሳካ አይችልም። እስከ አሁን ተጨባጭ ነገር እማይታየው የዝግጅት ችግር እንጂ የእውነት ችግር አይደለም። እውነት ካልሠሩበት ብቻውን እድገትን አያመጣም። ስለዚህ እውነት የተባለውን

[641] ይህን መሠረት በማድረግ የዋሽንግተን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ለአሥራ አምስት ዓመት ያለ ሕግ ሲሠራ ከቆየ በኋላ፥ በመጨረሻ አጣብቂኝ ውስጥ ሲገባ የገለልተኛ ቤተ ክርስቲያን ሕግ አምጥተው መተዳደሪያ በማድረግ የቤተክረስቲያንን ቀኖና በተግባር ተቃውመውታል። ከደንቡ አንቀጽ በከፊል።
[642] St Cyprian of Carthage, On the Church Select letters, p. 59
[643] The Challenge of Our Past, John H Erickson. P. 65

ነገር በሥራ መግለጥ ያስፈልጋል። በዚህ ታሪክ ውስጥ ያለፉትን አባቶች እውነት ለዘመናት ተጠብቆ ያገኘነው በመሆኑ ብቻ አይደ ለም። ለዚያ እውነት ውድ ሕይወታቸውን ሰጥተው ታሪክ የሠሩ ትን አትናቴዎስን፥ ቄርሎስን፥ ዮሐንስ አፈወርቅን፥ መመልከት በቂ ነው።[644] የእኛ አባቶች የያዙት እውነት፣ ከግለ ሰብ ድጋፍ ባሻገር መሆን አለበት፤ ያ ካልሆነ የምንሠራው ሁሉ የከንቱ ከንቱ ይሆንብናል።

## 5. <u>ጥንቃቄ ሊደረግባችው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች፤</u>

በምንሠራው ሥራ ሁሉ፣ ጥረታችን የተሳካ እንዲ ሆን፣ በቤተ ክርስቲያናችን ዙሪያ ለሚገጥሙን ልዩ ልዩ ችግሮች መፍትሄ ለማግኘትም ሆነ፣ በአጠቃላይ ሥራችንን በቤተ ክርስቲያኒቱ ቀኖና መሠረት ለማካሄድ ተገቢ ጥንቃቄዎችን ማድረግ እጅግ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው። ማድረግ ካሉብን ጥንቃቄዎች ዋና ዋናዎቹ ቀጥሎ ቀርበዋል።

### 5.1. <u>ከስሜታዊነት መላቀቅ፤</u>

በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የተሰበሰቡ፣ እንዲሁም በሩቅ ሁነው የሚ መለከቱ፣ አማኞችም ተቃዋሚዎችም አሉ። ዘመናዊው ፖለቲከ ኛም ለእርሱ አይሁንለት እንጂ በቤተ ክርስቲያን ላይ በመፍረድ ይሁንልኝ የሚለው ሐሳብም እንዳለው ይነግረናል። በዚህ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ አቅዋም ላይ ማተኮር ያስፈልጋል።

[644] *The Sven Ecumenicla Councils of the Undvided Church, The Council of Nicea and Creeds/Councils and Controversy.*



[645] አሁን ግን የሚታየው ከቀኖና ቤተ ክርስቲያንና ከእግዚአብ ሔር ክብር ይልቅ የሰዎች ጥቅምና ስሜት በልጦ እየታየ ነው። ይህ ደግሞ ለእድገታችንም፣ ቆምንለት ላልነው የሕግ ማስጠበቅ ሥራም፣ ትልቅ እንቅፋት ነው።

### 5.2. <u>ዘመኑን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥበብ መዋጀት፤</u>

እንዳለመታደል ሁኖብን የአባቶቻችንን የጠራ የሥርዓተ ቤተ ክር ስቲያን አቅዋም ይዞ ከመጓዝ ይልቅ ራእይ በሌላቸው ፖለቲከ ኞች ግፊት መነዳት ከፉኛ እየጎዳን ይገኛል። በዚህም ጉዳይ ከአ ሁኑ ጥንቃቄ ካልተደረገ አስመሳይ ፖለቲከኞች ራእያችንን ማጨ ለማቸው አይቀርም። የምናደርገው ጉዳይ ሁሉ ለቤተ ክርስ ቲያን የሚሰጠው ጥቅም ምን ይሆናል? በሚል መርሕ ላይ መመ ሥረት ያስፈልጋል። በማይጠቅም ወዳጅነት ላይ ተመሥርቶ መሥራት ውጤቱ፣ የቤተ ክርስቲያንን እድገት ከማቀጨጩም በላይ በታሪ ክም ተጠያቂ ያደርገናል።[646]

### 5.3. <u>ያልተጠኑ መግለጫዎች፤</u>

የግል አስተያየቶችና በአንድነት ዙሪያ የሚደረጉ የቃለ መጠይቅ ሂደቶች፥ ከግል ስሜት ጋር እንዳይጋጩ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በተለይም ከውጭ በሚመጣ ጫና ተመርኩዞ ያልተገናዘበ መልስ መስጠት ከቍጥጥር ውጭ ይሆንና ዓላማን ማዛባት ያመጣል። በየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን ሕገ ወጥ ናቸው ከሚባሉት ሳይቀር

[645] የግለ ሰቦችን ሐሳብ ስለ ተቃወመ ብቻ፥ ትናንት "ሐዲሰ ሐዋርያ" ያሉትን ቅን አገልጋይ ዛሬ አናውቅህም ማለት ለሕግ ቁመናል የሚለውን ጠንካራ አቋም ይቃረናል።
[646] John Meyenorff, Imperial Unity and Christian divisions. Pp. 20-28.

፣ ማናቸውንም የቤተ ክርስቲያን አባል ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ያስፈልጋል፡፤[647] ጥያቄ የጠየቀ ሁሉ፣ እንደ ተቃዋሚም፥ እንደ ደጋፊም መታየት የለበትም። ሁሉም ጥያቄ ትምህርት አለው ብሎ ማመን ያስፈልጋል።

## 5.4. ቤተ ክርስቲያን የምትታይበት ሁኔታ፤

ስደተኛው ሕዝብ ቤተ ክርስቲያንን የመረጋጊያ ቦታ አድርጎ ነው የሚመለከታት። በአንጻሩ የቤተ ክርስቲያን አቅዋምዋ ፍጹም መንፈሳዊ መሆን አለበት። ይህ ማለት የምንጠቀማቸው ቋንቋዎች ሸካራ ሁነው የሰውን ልብ ማሳዘን የለባቸውም። ልዩነት በሌሎች አግሮች አብያተ ክስቲያናትም መኖሩን ቀደም ሲል ተመልከተናል። በሌሎቹና በእኛ መካከል፣ ልዩ ሁኖ የተገኘው ሕገ ወጥ የተባሉትም፣ ሕጋዊ ነን የምንለውም፣ ሕግን ተከትለን አለመሥራታችን ነው።[648] አሁን ቆም ብለን ራሳችንን የምንመለከትበት ጊዜ ነው። ጥንቃቄ ስንል የቆምንበትን ዓላማ መከተል አለመከተላችንን እንድንመረምር የሚያደርገን መመዘኛ ማለታችን ነው።[649]

ሕዝብ፣ እኛ ሕገ ወጥ ናቸው የምንላቸውን ከፍሎች የተቃወመውና ስደተኛውን የተከተለው፥ ከስደተኛው እውነት አለ ብሎ ነው። ከእነሱ ያልተለየ ሥራ የሚሠራ ከሆነ ግን፣ እነሱን በሰደበበት አንደበቱ ስደተኛውንም መስደቡ አይቀርም። ይህ ደግሞ ለረጅም

[647] ችግር ያለባቸው ቤተ ክርስቲያኖች የችግራቸው መነሻ አባላቱን ካለማዳመጥና የአንድ ወገንን ሐሳብ በመደገፍ የሚደረገው ሂደት ነው። ለምሳሌ የሚሆኑ ሰነዶችን በዋቢ ሰነዶች ይመልከቱ።
[648] ዝኒ ከማሁ
[649] ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ አምስት ቍጥር 192



ጊዜ የተደከመበት ዓላማ ሜዳ ላይ ቀረ ማለት ነው። ውጤቱም ቆምንለት ያልነው የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ዓላማ ረጅሙ የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ሳይሆን፣ ሕገ ወጥ ናቸው ያልናቸው ሰዎችን መወዳደር ብቻ ይሆናል።[650] አሁን እንደምናየው የሚደረገው ያልተጠና ያስተዳደር ጣልቃ ገብነት፥ ጳጳሳት በቦታቸው ጳጳስ ካልሆኑ የት ሊሆኑ ነው? አንድ ቦታ የምእመናን ደጋፊ ስላለ ብቻ በሌላው ላይ ጣልቃ ገብቶ፣ አስተዳደራዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የቀኖና ድጋፍ የት አለ? [651] በየትኛው ቀኖና ነው ዕድሜ ብላጫ ስላለው ብቻ ያስተዳደር ጣልቃ ገብነት የሚፈቅድ መብት የሚሰጠው።[652]

ወደ እውነተኛው ቀኖና እንሂድና እንመርምር ካልን፣ ያለ ከፍሉ ጳጳስ ፈቃድ በሀገረ ስብከቱ ጳጳስ ላይ በንቀት ወይም በሌላ መንገድ ጣልቃ መግባት፥ ሕገ ወጥ መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ያስጠነቅቃል።[653] አሁን የሚሠራው ሥራ ከአባቶቻችን ቀኖና ጋር በፍጹም አይስማማም፤ ሌሎችን መናቅ፣ ከምእመናን ጋር ሁኖ ጳጳሳትን ማማትና ማቃለል በሙሉ፣ ሐዋርያትም፥ ሊቃውንትም፥ በጉባኤያት የደነገጉት ሕገ ቀኖና በፍጹም አይፈቅድም።[654]

ይህ አካሄድ፣ ቤተ ክርስቲያንን እያፈረሰ እንጂ እየጠቀመ አይደለም፤ ስለዚህ የውይይቱ ጥንቃቄ የሚጀምረው ቆምንበት ከምን

[650] የማይገለጥ የተከደነ የለም። ገጽ 50
[651] ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ አምስት ቍጥር 155
[652] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ አምስት ቍጥር 160
[653] *ዝኒ ከማሁ*

[654] ፍትሐ *መንፈሳዊ አንቀጽ አምስ ቍጥር 180-185 ያሉ አንቀጾች ይህን ያስረዳሉ።*

ለው ዓላማ በተቃራኒ እንዳይሆን፣ አብረን ከምንሠራው ጋርም ያለንን ግንኙነት መመርምር ያስፈልጋል። የቆምንበት ዓላማ ለራስ ስሜት ሲባልም አቅጣጫውን እንዳይስት ከአሁኑ በጥብቅ ሊታሰብበት ይገባል።

## 6. <u>ውይይቱ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ጥቅም፤</u>

ውይይቱ መቀጠሉ ለቤተ ክርስቲያናችን ብዙ ጠቀሜታ አለው። ቤተ ክርስቲያን ባለፈ፥ በአሁን፥ በሚመጣ፥ ታሪክ ላይ የቆመች ናት። ውይይቱም በነዚሁ መሠረቶች ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባል። ይህን ሐሳብ ለማዳበር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ የበዓለ ሢመታቸው ዕለት ባደረጉት ንግግር የዚህን ተመሳሳይ ሐሳብ አስቀምጠዋል። ቅዱስነታቸው በቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥለሴ በቤተ ክርስቲያኒቱ የተከናወኑትን ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች፣ በነጥብ በነጥብ ከዘረዘሩ በኋላ፣ የበዓሉ የክብር ባለቤት ይሆናሉ ያሏቸውን ሦስት አካላትን እንዲህ አስቀመጠዋቸዋል።

*“የዚህ ክብር ምክንያት ማረፊያ እኔ የክርስቶስ የኢትዮጵያ የግርማ ዊነትዎ አነስተኛ አገልጋይ ብሆንም፣ አድራሻው ለቤተ ክርስቲያን ስለ ሆነ፣ ተቀባይዋም ራሷ ቤተ ክርስቲያን ናት። በሦት ረድፍ ወገኖቿን አሰልፋ ይህን ክብር ትቀበላለች፤ በዘመናት መካከል ወደ እምነታቸው ምንጭ ለመድረስ ወደ እስክንድርያ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ተነሥተው በምድረ በዳ ወድቀው የቀሩ ኢትዮጵያውያን በአጸደ ነፍስ ሁነው አሁን የዚህ ክብር ተቀባዮች ናቸው። ለዚህ ክብር በዛሬው ዕለት ከአረጋዊው የቅዱስ ሲኖዶስ አባል እንሥቶ በጠረፍ ምድር፣ ሕፃናትን ፊደል እያስቆጠረ፣ በማሳደግ ላይ የሚገ*



*ኘውን ሽማግሌ የተሰፋ ሰንቅ አስይዞ በመሸኘት ለራሱ ደግሞ በእርሻና በሌላም ተግባረ ዕድ ተጠምዶ የሚውለው ካህን የዚህ ክብር ተካፋይ ነው። ለወደፊትም በዚች የክርስትና መዲና በምት ሆን አገር የሚነሡ አሁን በአምሳለ ዘር የሚገኙ ሁሉ የዚህ ክብር ተቀባይዮች ናቸው። ከዚህ ሁሉ በላይ የዚህ ክብር ተቀባይ የቤተ ክርስቲያን መሥራች ጠባቂዋም ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ ለተደረገው ክብር ሁሉ እንዴት አድርጌ በሚገባ መልከ አጸፋውን እከፍላለሁ? በማ ለት በጣም አልጨነቅም። እነዚህ ሁሉ የክብር ተካፋዮች ወሮታ ውንና አጸፋውን ለመክፈል አብረውኝ ስለሚሰለፉ በዚህ ተግባር ብቻየን አለመሆኔ እጅጉን ያስደስተኛል፤” ብለዋል።*[655]

ቅዱስነታቸው እንዳስቀመጡት ቤተ ክርስቲያን የአሁን ብቻ አይደለችም። ቤተ ክርስቲያን ያለፉት አባቶች አሻራ ጭምር ናት።[656] በዚያ ቅዱስ አደባባይ ላይ ሁነው የአደራ ኑዛዜ ነው ጥለው ያለፉት። ይህ ትልድ የሚወያይበት ነጥብ የሚጀምረው በኒህ ቅዱስ አባት ላይ ከተፈጸመው በደል መሆን አለበት።[657] ያለምንም ሕጋዊ የፍርድ ቤት ትእዛዝ በእሥር ቤት እንዳሉ ነው በግፍ የተገደሉት። እኒህ የቤተ ክርስቲያን ቅዱስ አባት ስለ ተገደሉበት ሁኔታ እንኳን ማን ተጠያቂ እንደ ሆነ፣ ምንም የተባለ ነገር አልነበረም።

---

[655] የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ከሚል መጽሐፍ የተወሰደ፤
[656] St Irenaeuse of Lyons, On the Apostolic Preaching, p. 42
[657] *የቋሚ ምስክርነት, አባ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ። ገጽ 69*

አስገዳዮቻቸው ግን የቀልድ ሐውልት አቁመው ደሙ በእጃቸው እያለ፣ ተሰብስበው *'ሰማዕት'* ማለት በቂ አለመሆን ብቻ ሳይሆን፣ ለሚያስተውለው ሰው ልብንም ያደማል። በዚያ ታሪካዊ አደባባይ ቁመው አደራ የሰጡት፣ ቤተ ክርስቲያንን እንዲመሩ የሚሾሙት ሁሉ፣ በሐዋርያዊ ቀኖና በመሆኑ ያም ቀኖናዊ ሹመት እንዴት እንደመጣና እንዴት መጠበቅ እንዳለበት፣ ለወደፊት የሚመጡት በዓሉን በመንፈስ ያከበሩትን ያህል እንዲሁም ሕጉን የማስጠበቅ ኃላፊነትም ጭምር እንዳለባቸው በማስገንዘብ ነበር።[658] በዓሉም የተከበረው ሕጉ የሰጠውን መብት በማስጠበቅ ነው፡፡

ቀኖናዊ ሕጉ ከተሻረ የእሳቸው ሹመትም እንዲሁ ተሸሯል ማለት ነው። በግፍ የሞቱት አባት ሞታቸው ግፍ ከሆነ፥ በግፍ የተሰደዱት አባትም ስደታቸው ግፍ ነው። ግፍ ፈጻሚዎቹ ስለ ተለወጡ ብቻ የግፍ አፈጻጸሙ የተለወጠ ይመስል ከተጠያቂነት ነጻ መውጣት አይቻልም።[659]

ያለፉት አባቶቻችን የከብራቸው ተከፋዮች መሆን ከቻሉ በግፍ ሲገደሉ፣ ቀጣዮቹ ሲሰደዱ አብረው ይደማሉ፤ የቅዱሳንን ኅብረት የምናምን ከሆነ፣ የቅዱስነታቸውንና ከሳቸው በፊት የነበሩት ያስቀመጡትን የእምነትና የሥርዓት አደራ ልናይ ይገባል።[660] እርሳቸው በዘመናቸው የተቀበሉትን ያን ኃላፊነት በብቃት በአደባባይ ተወጥተዋል። አባቴ ያሏቸው ልጃቸው፣ አብረው ታሥረውም፣ ከሞት ያመለጡ አባቶች፥ በአንድ ወይም በሌላ ሥራቸው ያን ታሪክ ቀብ

[658] የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፤
[659] የማይገለጥ የተከደነ የለም፤ ገጽ 31-33.
[660] የፍትሐ ነገሥት መቅድም ገጽ 10 ይመልከቱ።



ረዋል፤ በመቅበርም ላይ ይገኛሉ። ውይይቱ ይህ ተጠያቂነት የማን እንደ ሆነ በሀቀኝነት ለቀጣዩ ትውልድ የምናስተላልፈው ኃላፊነት ይሆናል።

አንድ ጊዜ ሙተዋልና አናንሣ የሚባል ከሆነ፣ አሁንም ስህተትን በሕጋዊነት ለመቀበል ያስችላል። ያን አባባል መጥቀሳችን ያለፈ ታሪክን ለአዲስ መቀስቀሻ እያነሣሣን አይደለም። ስህተት እንዳይደገም እያልን ነው እንጂ። ያን ስህተት ነው ካልን፥ ይህም ስህተት ነው፤ ይህ ስህተት ከሆነ መታረም አለበት፤ ዳግም እንዳይደገምም ማቆሚያ ሕግ ያስፈልጋል፡፡[661]

ቅዱስነታችው በንግግራቸው፣ እግዚአብሔር አብሮ ይሠራል ነው ያሉት። *"እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከናንተ ጋር ነኝ"* ይላል እግዚአብሔር። የክብሩ ተቀባይ እንደ ሆን ሁሉ፥ በዚሁ ልክ በምንሠራውም ጥፋት ያዝናል።[662] ስለዚህ ውይይቱ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ማን ለጥቅም እንዳዋለ፣ የፍርድ አደባባይ ነው። ይህ ጉዳይ በተለይ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ሕጋዊነቱን ከመናገር ያለፈ ሥራ መሥራት እንዳለበት ካመነበት፣ ትልቅ ታሪካዊ መረጃ ነው።[663]

ይህ ያልንበት ዘመን ምንም እንኳ ተደብቀው ቢሠሩት ለሠሪዎቹ ይምሰላቸው እንጂ ስውሩ ገሀድ የሚሆንበት ዘመን ነው ። ትናንት የአዲስ አበባው ሕገ ወጥ ተሿሚና የሲኖዶስ አባላት ከጊዜው

[661] እንደ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሄድ ማለት፣ ሦስቱ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ያስቀመጡትን ቀኖናዊ ሕግ መቀበል ያስፈለጋል ማለት ነው።
[662] የቍጥር 224 የግርጌ ማስተወሻን ይመልከቱ።
[663] የሰላም ጉባኤው ሪፖርት ለዚህ ትልቅ ድጋፍ ይሆናል።

ፖለቲከኞች ጋር አብረው ሠርተው በአደባባይ ይከዱት የነበረው ጉዳይ፣ ዛሬ በግልጽ አንድ አገር ብቻ ሳይሆን ዓለም ሰምቶታል።[664] ውይይቱ ይህንን እንኳን አንጥረን እንድናውቅ ይረዳናል። ቤተ ክርስቲያን ካለፉት ቅዱሳን ሕይወት፥ ተመክሮ፥ ትምህርት፥ ሥርዓት፥ ትውፊት፥ ላይ የተመሠረተች ናት።[665] በዚህ ጥናታዊ መጽሐፍም ሆነ በሌሎች ጥንታዊና የአሁን ዘመን ጥናቶች፣ እንደ ምንረዳው ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው፣ በየደረጃው ባለፉ ቀደምት ቅዱሳን ትምህርትና ሕይወት መሆኑ ይታወቃል።[666]

ውይይቱ ይህን ዙረን እንድንመለከት ይረዳናል። እየሠራን እንድና ስተምር፣ እያስተማርን እንድንሠራ ይረዳል፤ ይህን ማስጠበቅ ጠቅ ላላ እምነቱን ማስጠበቅ ማለት ነው፤ ይህ ካልሆነ የቆምነው ለሌላ ዓላማ ነው ማለት ነው። ውይይቱ ትክክለኛ ዓላማችንን እንድና ስረዳ ሰፊ ዕድል ይሰጣል። የተነሣንበት ዓላማ የነገረ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ እንጂ የዕለት ሥራ ማግኛ አለመሆኑን በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ፊት የምንመሰክርበት ትልቅ መድረክ ነው።[667]

ውይይትን የሚፈራ፣ እውነት የሌለው ሰው ነው። ከእውነት ላይ የቆመ ሰው ግን፣ በተወያየ ቍጥር እውነቱ እየነጠረለት ይሄዳል። እኛም እውነተኛ ለመሆናችን በቂ ጥናት ካደረግን ውይይቱ የእኛን እውነተኝነት፣ አደባባይ የምናወጣበትን ሁኔታ ያመቻችልናል።[668]

[664] የአቶ ታምራት ላይኔ ምስክርነት።
[665] ትምህርተ ዲዲስቅልያ ዘአበው ገጽ 16።
[666] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ በዲያቆን ያረጋል አበጋዝ ገጽ 24
[667] Barnes, Athanasius and Constantius, p. 82
[668] Ibid



ውይይቱ ድርጅታዊ ብቃታችንን ያጎለብታል። ከተጠያቂነትም ነጻ ያወጣል። በሐሰት የተቀመጡና ሐሰትን የሚያራምዱ ሰዎች ብዙ በመናገር ሰው ስለሚያሳመኑ፥ ለዚህ የተመደበ በቂ በጀትም ስላላቸው፥ ውይይቱ የሐሰት ከምራቸውን ይንደዋል።[669]

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ትልቁ ምሳሌያችን፣ ቅዱስ አትናቴዎስ ነው። አትናቴዎስ በተከሰሰበት ሁሉ የረታውና አሁን ቅዱስ የተባለው ለውይይት ባገኘው ዕድል እውነተኛነቱን ስላረጋገጠ ነው።[670] ውይይቱ ይህ ስህተት እንዳይደገም መሠረት ይጥላል፤ ቤተ ክርስቲያን የደረሰባት ችግር፣ ከባድ ቢሆንም ከችግሩ ግን ብዙ ተምራለች፤ ከላይ ለዚሁ በተሰጠው ቦታ ላይ በሰፊው እንደ ተገለጠው፣ ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋትና መጠናከር፣ በቤተ ክርስቲያን የተፈጠረው ችግር ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።[671]

አሁን ለዋቢነት የምንጠቅሰው ሕግ፣ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ለመምራት በምታደርገው ጉዞ በገጠማት ችግር ተመሥርቶ የተዘጋጀ ነው። ከአሁን በኋላ የሚመጣ ትውልድ እኛ በሄድንበት የችግር መንገድ መሄድ ስለሌለበት፣ ቤተ ክርስቲያንም በዚህ ምክንያት በየጊዜው ግራ መጋባት ስለሌለባት፣ አሁን የሚደረገው ውይይት ለቤተ ክርስቲያን ህልውና ቀዋሚ የሆነ ሕጋዊ ዋስትናን ያስገኛል። ጠቅለል ባለ መልኩ ውይይቱ የቤተ ክርስቲያንን ያሁንና የመጭውን ዕድል የሚወስን ይሆናል።

[669] Creeds/Councils and Controversies, Documents illustrating the history of the church. pp. 59-61
[670] Ibid
[671] Ibid

ይህን ሐሳብ እንዲህ ብለን ልንደመድመው እንችላለን። የአንድነት ውይይቱን ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በማመን፥ መሠራት ያለባቸው ሥራዎች ግን ዓላማችንን እንዳያስቱን ከመጠንቀቅ ጋር ሕዝቡም የድርሻውን እንዲወጣ እያስተማርን እውነት የሆነውን የቤተ ክርስቲያን ሕግ ማስጠበቅ ያስፈልጋ። ከዚህ ጋር ይህን እያደረግን የምናተኩርበት አቅጣጫ ምን ይሁን? የሚለውም ሌላው አጠያያቂ ጉዳይ ነው። ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ከዚህ ቀጥሎ ሰፋ ባለ መልኩ ማብራሪያ ይቀርባል።



# ክፍል አምስት፤

# የቤተ ክርስቲያን የወደፊት ራእይ

ባለፉት አራት ዐበይት ክፍሎች በዝርዝር ከቀረበው ገለጻ፣ለመረዳት የቻልነው፤ ቤተ ክርስቲያናችን የተለያዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮች እንደነበሩባት፣ አሁንም እንዳሉባትና ወደፊትም ሊገጥሙአት እንደሚችሉ ነው። በመሆኑም፤ ያሉባትን ችግሮች ለማስወገድ ጉዳዩ እሚመለከተን ሁሉ፣ ስህተቶቻችን ምን እንደሆኑና እነሱንም ለማስወገድ እንድንችል፣ የወደፊት ራእይ ሊኖረን ይገ ባል።ስለዚህ *“የቤተ ክርስቲያን የወደ ፊት ራእይ”* የሚለው ዐቢይ ርእስ ቀጥሎ በተመለከቱት ሁለት ርእሶች መነሻነት በቂ ማብራሪያ በቅደም ተከተል መመልከት ይቻላል።

1. አቅጣጫ መርና ሥራ አነሣሽ ነጥቦችና
2. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳቦች፤

በሚሉ ሁለት ንዑሳን ክፍሎች ገለጻው ይቀርባል።

## 1. አቅጣጫ መርና ሥራ አነሳሽ ነጥቦች፤

በዘመናት ለክርስቲያን ከባዱ ነገር እውነት የሆነውን ወንጌል በማስተማራቸው ምክንያት፥ አገርን ጥሎ መሰደድ ነበር። ዋናው ቁም ነገር ግን ክርስቲያኖቹ ስደቱን ለቁም ነገር መጠቀማቸውና፥ በዚህ ምክንያት ክርስትና መስፋፋቱ ነው። የእኛ ቀደምቶች ስደትን ቤተ ክርስቲያንን ለማስፋፋት ተጠቅመውበታል። ራሳቸውን ለማስተማርና ጥንካሬያቸውን ለመፈተሽ ረድቷቸዋል። የተቀበሉት አደራ የዘላለም ሕይወትን የሚያስጥ ሰማያዊ ጸጋ እንዳለው ስለቈጠሩ፣

የተሰደዱበትን አገር እንደ ትውልድ አገራቸው፥ሕዝቡንም እንደ ሕዝባቸው በማድረግ ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ እየሠሩ የተቀበ ሉትን አደራ በታማኝነት ተወጥተዋል።[672]

አሁን ባለ ታሪኮቹ እኛ ሁነናል። እንደ አባቶቻችን እኛም በሃይማ ኖታችን ምክንያት ተሰድደናል። አሁን በስደት ላይ ሁነን የእግዚ አብሔርን አደራ እንድንወጣ ዕድሉ ተሰጥቶናል። ስለ ስደቱ ስና ጠና ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያው ምእት ዓመት ጀምራ እንደ ቋሚ ሁና መቀጠሏን እንማራለን።[673] የዚህ መጽሐፍ ዓላማም፣ በአንድ በኩል የተሰደድንበትን ዓላማ እንድናውቅ፣ ከታሪክና ከት ውፊት ማስተማር ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የምንሠራውን እየ መረመርን በዕቅድ እንድንሠራ ማድረግ የምንችልበትን መንገድ ማሳየት ነው።

በዚህ ምክንያት ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ሥራውን ጀምሮ በመን ቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ሥራው የተሳካ ይሆን ዘንድ አንዳንድ ዕቅድ መውጣቱ አይቀሬ ነው። ይኸን መሠረት በማድረግ ነበር ከዚህ ቀደም ቶሮንቶ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ በተካሄደው የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ፣ ባለ ሦስት ነጥብ ሥራ አነሣሽ ነጥ ቦችን አቅርቦ የነበረው። የሦስቱ ሥራ አነሣሽ ነጥቦችንም ምክን ያት በማድረግ በሦስት አቅጣጫ የሚሠራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ነበር።

ከኮሚቴዎቹ መካከል የውስጥና የውጭ የሰላም ኮሚቴ፣ ሥነ ጽሑፍና ጥናት ከሚቴ፣ በመባል ተሰይሞ ነበር። ከጥናትና ሥነ

[672] Apostolic Fathers, Volume I, Clement of the Rome
[673] የሐዋ 8፡ 1-5



ጽሑፍ ኮሚቴው፣ ከዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ጋር የተመደቡት ሰዎች መካከል ገሚሶቹ በሥራው ስላልተገኙ፣ በዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ አማካይነት አንድ <u>መጽሐፍ</u> ተዘጋጅቶ መቅረቡ ይታወሳል።[674] ሁኖም በዚያ ጊዜ የቀረቡት <u>ሌሎቹ</u> ሦስት የሥራ አነሳሽ ሐሳቦች አሁንም ድረስ መልስ ስላላገኙ እንደ ገና መታየታቸው አስፈላጊ ሁኖ ተገኝቷል። የሐሳ ቦቹ መነሻ ጥያቄ ጉዟችን ወዴትና እንዴት መሆን አለበት? ከሦስቱ አንዱን መምረጥ የሚል ነበር። እነዚህም አማራጭ ሥራ አነሣሽና ዓላማ መር ነጥቦችም የሚከተሉት ናቸው።

1.1.. <u>እንደ ተሰደዱ ለየግል መኖር፤</u>
1.2.. <u>ስደትን ቋሚ አድርጎ በአንድነት መኖር፤</u>
1.3.. <u>በስደት ሁኖ ለአንድነት መሥራት፤</u>

***<u>የስደት ምርጫ፤</u>***

*ሊቀ ጳጳስ ካሊስቶስ፤ "የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን"* በሚል ርእስ መጽሐፋቸው ላይ እንዲህ የሚል አባባል አስቀምጠዋል። ***"የትኛውም የባዕድ አገር እናት አገር ነው፤ የትኛውም እናት አገር የባዕድ አገር ነው"።***[675]

ይህ አባባል ለክርስቲያኖች በባዕድ አገር ቢኖሩም አገራቸው ነው። በትውልድ አገራቸው ቢኖሩም ባዕድ አገር ነው ማለት

[674] *ሕጋን ጥሶ ሕጋዊ መሆን ይቻላልን? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አካሄድ በኦርቶዶክሳዊ ቀኖና ሲታይ።*

[675] *Timothy Ware,The Orthodox Church, p. 172*

ነው። ዋናው በዚያ አገር ኑረው የሚሠሩት ሥራ ነው ልዩ የሚ ያደርገው። ስለዚህ የሚሠራው ሥራ እንዴትና ለምን? የሚለው ጉዳይ ሊያሳስባቸው ይገባል። በመሆኑም መርጠው የሚቆሙበት ዓላማ ወሳኝነት አለው።

ስለዚህም እኛን ምንጊዜም ተጠያቂ የሚያደርገን በባዕድ አገር መኖራችን ሳይሆን የሠራነውና እየሠራነው ያለው ተግባር ነው። በአገር ከሚኖሩት የምንለየው በሥራ እንጂ በስደት አይደለምና። በሕጋዊ መንገድ ሠርተን የምናሳየው የሥራ ውጤት ነው፤ ልዩ የሚያዳርገን። እናም ስደቱን እንዴት ነው እየተጠቀምንበት ያለ ነው? የትኛውንም ምርጫ እንምረጥ፣ የምንመርጠው ምርጫ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት።[676] ኦር ቶዶክስ የሚያሰኘው ያ ነውና። ያ ካልሆነ ቤተ ክርስቲያንን ለጊዜ ያዊ መጠለያና ጊዜ ማሳለፊያ እናደርጋለን እንጂ የቤተ ክርስቲ ያንን እምነት አስጠብቀን ለእግዚአብሔር መንግሥት ቁመናል ማለት አይቻልም። ስለ ሆነም ምርጫችን ምን ይሁን?

## 1.1 <u>እንደ ተሰደዱ ለየግል መኖር፤</u>

እንደ ተሰደዱ በየግል መኖር ማለት፣ ስደትን መሠረት አድርጎ ግን ለእንጀራ መኖር ማለት ነው። ምርጫውና አካሄዱ፥ እንደ ማንኛውም የኢኮኖሚ ስደተኛ ግለሰብ የሕይወት ፍጻሜ እስኪደርስ ድረስ መኖር ነው። ይህን ምርጫ ከመረጥን ስለ

[676] TheSeven Ecumenicla Councils of the Undvided Church the Council of Nicea and Creeds/councils and controversis.



ወደፊት ማሰብ አስፈላጊ አይደለም። በዚህ መርሕ የምንሄድ ከሆነ፣ በዓመት ሁለት ጊዜ የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በመሰብሰብ፣ መግለጫ ማውጣት፤ ቃለ ጉባኤ መያዝ አስፈላጊ አይደለም።

አሁን እየሆነ እንዳለው ሁሉ ፣ እያንዳንዱ የግል ቤተ ክርስቲያን በመያዝ እንደ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን እንደ ግል ንብረት በመጠቀም መኖር፣ ሲሞት ቤተ ክርስቲያን የመቀበሪያ ቦታ ካለው መልካም፣ ከሌለው ግን አስፈቅዶ መቅበር። አሁንም የምናየው ይህን መርሕ ነው። ለታሪክ ግድ ከሌለን ለሚጠፋው ጥፋት ተጠያቂነት የማይሰማን ከሆነ ከዚህ ሌላ ያለ አይመስልም። ስለ ሆነም በዚህ መርሕ ከተሄደ ራእዩም ከዚያው አብሮ ይቀበራል፤ ይህም አንድ ምርጫ ነው።

ይህ ከሆነ ምርጫችን ብዙም የሚያሳስብ ጉዳይ አይሆንም፤ እስከ ጊዜ ሞት ቆይቶ ማለፍ ብቻ ነው፤ ለተተኪው ትውልድ ትምህርት ቤት ማቋቋም፣ እምነትን ማስጠበቅ፣ ለሌሎች መትረፍ፣ አሳሳቢ ጉዳይ አይደለም። ለዚህ መርሕ አሳሳቢው ጉዳይ ጠቀም ያለ ገንዘብ አግኝቶ፣ ወደ ንግዱ ዓለም መግባት፣ የተለያዩ የገቢ ማግኛ ዘዴዎችን በሌሎች ስም ማቋቋም፤ እስኪሞቱ ገንዘብን ማጠራ ቀም፤ ሲሞቱ የተጠራቀመውን ገንዘብ መንግሥት እንዳይወስደው ለመቃብር አዋልኩት ብሎ፣ ቀሪው ሰው ከማስፈቀድ በቀር ሌላው ጉዳይ አሳሳቢም አስጨናቂም አይደለም።

ይህ ምርጫ ከሆነ፣ ስደተኛ ሲኖዶስ የሚለውን ሐሳብ ማንሣት ማታለል ይሆናል። መግለጫ ለማውጣት በየዓመቱ ምእመናንን ማስቸገርም አስፈላጊ አይደለም። ሲኖዶስ የሚለውን ስም፣ ከዚሁ ላይ ማቆሙ ይመረጣል። አንዳንድ የሚታዩ ምልክቶች ሲኖዶስን

ሲኖዶስ የማያሰኙ ሂደቶች ናቸው። ፖለቲካ የተፋቸው ገለሰቦች ለመሰብሰቢያነት በዙሪያው እያንዣበቡ ይታያሉና የሲኖዶሱ ህልውና ሊታሰብበት ይገባል ። አሁን በሚደረገው ሁኔታ ከቀጠለ ራሱ በስብሰባ መገናኘትም የሚከብድ ይመስላል፣ ይህን መንገድ ከመረጥነው እስካሁን ባደረግነው ሁሉ ሕዝቡን ይቅርታ መጠየቅ ይኖርብናል። ምክንያቱም የማናደረግውና የማይሆን ነውና። ስናወራ የኖርነው የራስን ስሜት ለመግለጥ ሌሎችን ሕገ ወጥ ማለት፣ ነገር ግን ሕጋዊ ሥራ አለመሥራት፣ የግለሰቦችን ጥቅም ለማስጠበቅ በመጣር የቆሙበትን ዓለማ ንዶ አናውቅም በማለት በተቃዋሚነት መቆም ምን ይባላል?

ሐሳብ እንኳ ማሰብ ካልተቻለ፣ ከዚህ የተለየ ምርጫ አለ ማለት ቢቻል እንኳ ተግባሩ ሊያስኬድ አይችልም። ይህ አንድ ምርጫ ነውና። ነገር ግን ምርጫችን ይህ ከሆነ እስካሁን የባከነው ጊዜ ሳይቆጠር፣ ወደፊት መቀጠል አይኖርም። ይህን እንደ ዋና ምርጫ ከወሰድነው፣ መረሳት የሌለበት ጉዳይ፣ የአዲስ አበባውን ሲኖዶስ ሕገ ወጥ ነው ለማለት የልብ ድፍረት፥ የአእምሮ ጉልበት፥ የሕሊና ነጻነት፥ አይኖረንም። ምክንያቱም የመረጥነው ምርጫ የኢኮኖሚ ስደት እንጂ የሃይማኖት ባለመሆኑ ነው። ይህ እንደ ምርጫ ካልተወሰደ ምን ይመረጥ? ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅምና የሚያዋጣ ከሆነ ሁለተኛውን ምርጫ እንመልከተው።

## 12. <u>ስደትን ቋሚ አድርጎ በአንድነት መኖር፤</u>

ይህ ማለት፣ በስደት ያለችው ቤተ ክርስቲያን፣ ከአገር ቤቱ ጋር ምንም የሚያገናኛት ነገር ሳይኖር ራሷን አስችሎ፥ ራሷን የቻለች ቤተ ክርስቲያን አድርጎ መኖር ማለት ነው። ይህ በዚያ ጊዜ



የቀረበው አሁንም መልስ ያላገኘው ምርጫ ነበር፤ ይኸኛው ምርጫ ከተመረጠም ብዙ የቤተ ክርስቲያንና የመጽሐፍ ቅዱስ ተምሳሌቶች አሉን፤
ከአብርሃም ታሪክ እንኳ ብንነሣ ከአገሩ ሲወጣ፣ ከወገኑ ሲለይ አንድ ዓላማ ነበረው፤ ዓላማውም እግዚአብሔርን ማክበር ነበር። እግዚአብሔር *"እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርግሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህን እባርካለሁ፣ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።"* በማለት ይህንን በረከት ሲያሸከመው ለዚህ ቃል ኪዳን ታማኝ ሁኖ ኑሯል።

ለጊዜው ቃል የተገባለትን ምድር ባያገኝም፥ ሕይወቱን በሙሉ በእንግድነት ቢያሳለፈውም፥ እሱ ግን በእምነት እግዚአብሔርን እያከበረ ኖረ። ዓላማውን አላዛነፈም፤ ልጆቹም ያንኑ ፈለግ ተከት ለው ሄዱ። ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ የተሰጣትን፣ አደራ ትወጣ ዘንድ ክርስቶስ እንዲህ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል። *"በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። በአንዲቱ ከተማም መከራ ቢያሳዩአችሁ፣ ወደ ሌላዪቱ ሽሹ፤ እውነት እላችኋለሁና፤ የሰው ልጅ እስኪመጣ ድረስ የእሥራኤልን ከተማዎች አትዘልቁም።* [677]

ይህም የክርስቲያኖች አገራቸው የሚያመልኩት አምላካቸው መሆኑን ያመለክታል። ከላይ በጥቅሱ በተገለጸው መሠረት፣ ስለዚህ ሰዎች የሚኖራቸው አገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ

[677] *ማቴ 10፡ 22-23*

የሚያደርጉበት እንጂ፣ የዜግነት ጉዳይ አይደለም። [678] አሁን በዘመናችንም ይህን መርሕ ተከትለው የሚሠሩ ክርስቲያኖች አሉ። የእኛ ስደትም በአገር ላይ በነጻነት ማከናወን ያልቻልነውን ክርስቲያናዊ አገልግሎት እያገለገልን ነው።[679] ጉዳዩን ከአገር ጋር እንዲያያዝ ያደረገው ነጻነት የለም በማለት ነው። ይህ ማለትም ቤተ ክርስቲያን ከምታከናውነው አንደኛውና ዋናው ሥራዋ፣ የአባሎቿን ይቅርና የሰው ልጆችን ሁሉ ሰብአዊ መብትና ነጻነት ማስጠበቅ ስለሆነ ነው። በዚህ በሁለተኛው ምርጫ መርሕ የምንኖር ከሆነ፣ የሚከተሉትን ነጥቦች ግብ አድርጎ መነሣት ያስፍልጋል።

## ቀኖናዊ ሕግን መከተል፤

በቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንደምንመለከተው እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያንን የክርስቶስ አካል የሚያሰኛት ምን ምን ስታሟላና እንዴት ስትሠራ ነው? ለዚህ ጥያቄም ቀኖናዊ መልስ የሚገኘው እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በተበታተነ መልኩ እንደ ንግድ ኩባንያ ለብቻ ፈቃድ አውጥቶ ብቸኛ ሁኖ ሊሆን አይችልም። አንድን ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን የሚያሰኘው ቀኖናዊ ሕግ በሁለት መንገድ ይገለጣል።

<u>አንደኛው፤</u> እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን <u>አንድ ፈቃድ</u> በማውጣት አንዲት ቤተ ክርስቲያን በመሆን በቅዱስ ሲኖዶስ በተመደበላቸው ጳጳስ እየተመሩ መኖር ማለት ነው። ዕውቅናው በአንድ ፈቃድ ሆኖ፣ ኢትዮጵያዊት አሜሪካዊት አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በማለት መሰየም ሲቻል ነው።[680] ለምሳሌ እንደ ግብፅ፣ እንደ ግሪክ፣ እንደ ሩሲያ፣ እንደ ካቶሊክ፣ አብያተ ክርስቲያናት ማለት ነው።

<u>ሁለተኛው፤</u> ሕጋዊ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን መሠረት ያደረገ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የየራሱ መተዳደሪያ ደንብ እንዳለ ሆኖ፣ በሲኖዶሳዊ ምልዓተ ጉባኤ የተመደበለትን ሊቀ ጳጳስ ሲቀበል፣ በዚያው በተቀበለበት ሰዓት የሲኖዶሱ አባል በሆነው ጳጳስ አማካይነት አንድነቱን መሥርቷል ማለት ነው።

ከላይ የተገለጸው መርሕ ከመበታተን የሚያድን መርሕ ነው። ትምህርቱም፥ ጸሎቱም፥ ሥርዓተ አምልኮቱም፥ የተጠበቀ/የጸና፣ የጠራም ይሆናል። ይህ ሥርዓት የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ትጠቀምበት የነበረ ሥርዓት ነው።[680] አንዲት ቤተ ክርስቲያንን ቤተ ክርስቲያን የሚያሰኛት ሕጋዊ የክህነት ውክልና ባለው ሊቀ ጳጳስ መሪነት፣ ክህነታዊ አገልግሎት የምታካሂድ ቤተ ክርስቲያን፥ የሊቀ ጳጳሷ ከሲኖዶስ ጉባኤ አንድ መሆን ቤተ ክርስቲያኒቱን አንድ ያደርጋታል።[681]

በመሆኑም የእነዚህ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ጳጳሳት ጉባኤ አንድነት፣ በሁሉም ያለች አንዲት ቤተ ክርስቲያን ያሰኛታል።[682] ያ ከሆነ፣ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚከተሉት መዋቅሮችና ተቋዋሞች ያስፈልጓታል። ሁኖም ግን አሁን በድጋፍ ሰጭነት እንሰበሰባለን

[678] *የሐዋ 6፡*
[679] *ነጸብራቅ የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ ርእሰ አንቀጽ ይመልከቱ።*

[680] Ibid
[681] Metropolitan JOHN d. Zizioulas, The One and the Many. P. 49
[682] Ibid

የሚሉት ወገኖች፣ በድጋፍ ስም በጳጳሳት መካከል መግባት ማለት ፣ መደገፍ ሳይሆን መጣል ነው፥ ማክበር ሳይሆን ማዋረድ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ድጋፍ ለቅዱስ ሲኖዶስም ለቤተ ክርስቲያንም ስለማይበጅ መወገድ አለበት።[683]

በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት፣ የሊቃነ ጳጳሳትን ሥልጣን በእኩልነት ተቀብሎ፥ እነሱ በፓትርያርካቸው ሰብሳቢነት የሚያካሂዱትን ስብሰባና ውሳኔ መቀበልና ማክበር ነው፤ የማይናጋ የአንድነት መሠረት የሚሆነው።[684]

ጵጵስና የውትድርና ሥልጣን አይደለም። የሹመት ቅድሚያ ከሌላው ጳጳስ የተለየ ክብር ሊደረግለት የሚገባው በስብሰባ ጊዜ የሚሰጥ የመቀመጫ ደረጃ ብቻ ነው።[685] ያም ቢሆን የተመደበበት ሀገረ ስብከት ደረጃ ይወስነዋል። አንድ ጳጳስ በጵጵስና ከተሾመበት ቦታ ጳጳስ ነው።[686] ያለሱ ይሁንታና እርሱ ሳይጠየቅ በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ምንም መደረግ አይቻልም። ቀደምት አባቶቻችን በደነገጉት ድንጋጌ በወሰኑት ውሳኔ መሠረት፣ እያንዳንዱ ሊቀ ጳጳስ በሀገረ ስብከቱ ሥልጣኑ ፍጹም ነው።[687]

ጳጳስ ቢሳሳት፣ የሚታየው በፓትርያርኩ መሪነት በሚደረግ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ብቻ ነው።[688] ይህ ቀኖናዊ ሕግ ነው

---

683 የድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ የሲኖዶስ አስተዳደራዊ መዋቅር ተብሎ የቀረበ ሰነድ

684 *Richard R. Gaillardetz, by Wtha Authority. p. 69*
685 *ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት ቍጥር ኀምሳ ገጽ 30*
686 *ዝኒ ከማሁ*
687 *ዝኒ ከማሁ*
688 *ዝኒ ከማሁ ገጽ 33*



መሠረታዊ አንድነት የሚያመጣው። የእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ያስተዳደር ነጻነቱ ተጠብቆለት፣ ነገር ግን የበላይ የሆነው ጳጳስ የሲኖዶሱ ጉባኤ አባል በመሆኑ ምክንያት ቤተ ክርስቲያኒቱ በሊቀ ጳጳሰዋ አማካይነት አንድነት ትመሠርታለች።[689]

ይህ መርሕ በብዙ መልኩ፣ ቤተ ክርስቲያንን ቤተ ክርስቲያን የሚያሰኝ፣ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትን የሚያስከብር ነው።[690] ይህ ከሆነ ለአስመሳይ ፖለቲከኞች ቦታ የለም።[691] ለእውነተኛ አገር ወዳድ ፖለቲከኞችና ለእውነተኛ ክርስቲያኖች ግን፣ ቦታም፥ ክብርም፥ ሥራም፥ አለ። ይህንንም በሥራ ለመተርጎም ታጥቆ መነሣት፥ የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ያህል ቀጥሎ የቀረቡትን መነሻ በማድረግ መሥራቱ ጠቃሚነት ይኖረዋል።

### ሀ/. ወጥ የቤተ ክርስቲያን መመሪያ፤

ገልበጥባጣ ባሕርይን ከአባቶቻችን የሚያርቅ ቀዋሚ የሆነ የቤተ ክርስቲያን መመሪያ ያስፈልጋል። መመሪያውም የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮና ሥርዓት የሚያስጠብቅ እንዲሆን ያስፈልጋል። የሚወጣው መመሪያም ጥንታዊ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን መሠረት ያደረገ እንጂ፣ የግል ስሜታቸውን በቤተ ክርስቲያኒቱ ጣልቃ ለማስገባት የሚጥሩ ግለ ሰቦች ተሰብስበው መመሪያ እናወጣለን

---

689 *ዝኒ ከማሁ*
690 *ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ አራት ቍጥር 40 ኒቅያ*
691 *ለድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ አይነቶቹ ማለት ነው።*

ቢሉ፣ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም።[692] የወሚጣው መመሪያና ሕጉ መሠረት ማድረግ ያለበት የጥንት ቀኖናን፣ የአሁኑን ቃለ አዋዲና በቃለ አዋዲው ሥር የወጡ ወስጠ ደንቦችን መሆን አለበት። ያን ካደረግን ነው፣ ጥንካሬ ያለው ሕጋዊነትና እድገት የሚመጣው። ወጥ መመሪያ ማለትም ቀኖናዊ ሕግ ማለት ነው። [693] የጠሉትን ሰው በሽማግሌዎች እያመካኙ መጉዳት ግን ትልቅ ወንጀል ነው። [694] አሜሪካን አገር ሁኖ የሰውን ሰብአዊ መብት የሚጎዳ ሕግ አወጣለሁ ብሎ ማሰብ በራሱ የጤና አይመስልም።

ለ/. <u>የትምህርት ተቅዋም፤</u>

*"ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ"።* [695] ተብሎ እንደ ተጻፈ። እንደ ሌሎች አገሮች ምእመናን ሁሉ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንም ቋሚና ወጥ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀት ያስፈልጋቸዋል። ትምህርቱ ከምን ይጀምር የሚል መርሕም ሊኖር

*[692] ዲሲ ላይ በተካሄደው 33ኛው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ወቅት የተደረገውን መመልከት በቂ ነው። ቤተ ክርስቲያን እንኳ በቅጡ ገብተው ያማያውቁ በሲኖዶስ ተሰብሳቢዎች፣ በአንጻሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ታሳሪና ተሳዳጆች፣*
*የሎሰአንጀለሰ ድንግል ማርያም፥ የደቡብ አፍሪካ ቅድስት ሥላሴ፥ የአውትራልያ አብያተ ክርስቲያናት፥ ያወጡት መግለጫ በቁጠሮ ድጎረ ገጽ መመልከት ለዚህ በቂ መረጃ ነው።*

ለዚህ ተብሎ ነበር ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በአንድነትና በሕጋዊ መንገድ ለማስተዳደር የወጣ ውስጠ ደንብ በሚል እንዲወጣ የተደረገው። ይህ ሕግ በአትላንታ ቅድስት ማርያምና በዋሽንግተን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የቦርድ ሊቃነ መናብርት እንዳይሠራ ተደርጎ፣ በብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ተደግፎ፣ እስከ አሁን በሥራ ላይ አልዋለም። የሚገርመው ይኸው ሕግ በካናዳ በሥራ ላይ ውሎ በእነ አቡነ መልከ ጼዴቅም ተደግፎ ቤተ ክርስቲያንን ከወያኔ ከስ አድኗል።

የድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ ያወጣው መመሪያ፤ ገጽ

[695] የ.ሐ.ሥ 17፡ 11



ይገባል።[696]* ይህ መርሕ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ይካሄድ የነበረ ሲሆን ትምህርት፣ ምእመናን ወደ ተለያየ እምነት፣ እንዳይሄዱ ያደርጋቸዋል። የራሳቸውን ካወቁ፣ ሌላውን መከላከል ይችላሉ። የቤተ ክርስቲያን ቋሚ ሥራም የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት በትምህርተ ወን ጌል ማጠናከር ነው።

ሁሉም ሰው የክርስቶስን አዳኝነት ማወቅ አለበት። የጳራቅሊጦስ ዕለት ያስተማረውን የጴጥሮስን ትምህርት ስንመለከት፣ እግዚአብ ሔር ያዘጋጀው የማዳን ሥራ በነቢያት የተመሰከረ፣ እንደ ነበር በማስረገጥ ያስተማረው ትምህርት አጠር ያለ፥ ግን ሁሉ የተካተ ተበት ግሩምና ድንቅ የሆነ ትምህርት ነበር።[697] የዚህ ዓይነት ትም ህርት ለየዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያንም ያስፈልጋታል።

ክርስትና የመጽሐፍ ሃይማኖት ስለ ሆነ፣ ለማመን መጽሐፉ መጠ ናት አለበት። ለዚህም ደግሞ ወጥነት ያለው፣ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀት፣ ከሁሉ በፊት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ሥራ ነው። [698] ምእመናን የሚያምኑትን ካላስጨበጧቸው በእምነት መቆም አይችሉም። እንግዲያውስ ምእመናን ጸንተው እንዲቆሙ፣ የሚ

[696] የግብፅን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት፥ የአሜሪካን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት፥ በምሳሌነት መውሰድ ይቻላል።*modeals Curriculum for preparation of Sunday School sefvante by Victor Hanna ande the Orthodox Church in America from volume I- Vii Hand Books on the Orthodox Church

*[697] ዝኔ ከማሁ*

*[698] የዮሐንስ ወንጌል ም 5፡46-47*

ማሩበት ሥርዓተ ትምህርት ማቀድና ማዘጋጀት፣ ከሚሠራው ሥራ ሁሉ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ብርቱ ጉዳይ ነው።

ሐ/.<u>ልጆች በተወለዱበት ቋንቋ የሚማሩበት ሥ/ት. ማዘጋጀት</u>፤

ለቀጣዩ ትወልድ የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት መቋቋምና አገር በቀል አማኞች የሚቀርቡበትን መንገድ ማመቻቸት ሊታለፍ የማ ይገባው ታላቅ ኃላፊነት ነው። አሜሪካን አገር ያሉ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትን ምሳሌ (ሞዴል) ማድረግ ይቻላል። ለም ሳሌ አርመን ኦርቶዶክስ፥ ግሪክ ኦርቶዶክስ፥ አሜሪካን ኦርቶዶ ክስ፥ ያደጉት በዚህ መንገድ ነው።[699]

ለማደጋቸው ምክንያት የሆነው ልጆች በተወለዱበት ቋንቋ መማ ራቸው ነው። በተለይም የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ ጠንካራው ቤተ ክርስቲያን ነው። ካህናቶቻቸውን ክህነት እንዲ ሰጡ የሚያደርጉት፣ ቢያንስ የሥነ መለኮት ድግሪ ያላቸው ሲሆኑ ብቻ ነው። እንደዚያ ዓይነት ካህን ለማግኘት፣ ልጆች ከአምስተኛ ክፍል እስከ ዩንቨርሲቲ ድረስ ሳመር ካምፕ ስላላቸው ደኅና ካህን የሚሆነውን መርጠው ለማሠልጠንና ካህን ለማድረግ ችግር የለባ ቸውም። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ማድረግ መቻል አለ ባት።

ይህ መርሕ ደግሞ መሆን ያለበት፣ አሁን ነው። ነገር ግን ለዕለት ጥቅም በመወጋገዝ የነገው ሥራ ከተረሳ፣ አሁን ቤተ ክርስቲያንን

---

[699] ሁለት መቶ ሰድሳ አንድ የግርጌ ማስታወሻን ይመልከቱ።



እየቀበርናት እንጂ እያገለገልናት ነው ማለት አይቻልም። በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን የእኔ ልምራት ጦርነት ምን ለማደረግ ነው? በሳምንት አንድ ጊዜ ተሰብስቦ ምእመናን የሰጡትን ገንዘብ ለመ ቍጠር ከሁለት በላይ ሰው አስፈላጊ አይደለም። እንዲህ ዓይነት ቋሚ ሥራ ካልተሠራ ኮሚቴውና ሥልጣኑ ምን ሊያደርግ ነው? ስለዚህ እንደ ተሰደዱ በአንድነት መኖር የሚለው አማራጭ ከተ መረጠ፣ ካህናትን ማፍራት ያለብን ከዚሁ ነው።

ይህን ሐሳብ በሌላ ቋንቋ ብናስቀምጠው፣ በውጭ አገር ያለቺው ቤተ ክርስቲያን ራሷን የቻለች ቤተ ክርስቲያን ሁና መቀጠል የም ትችልበትን እድል ማመቻቸት ማለት ነው። አሁን በገለልተኛ የሚኖረው ሕዝብ ግን፣ ገለልተኛ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ እንኳ፣ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ስም የለውም። ቀዋሚ ሥራ ለመሥራት ከዚህ ወዴት ነው የምንሄደው? ነገ ማን ይተካል? ማለትን ይጠይቃል።

በየቤቱ ያለውን ልጆችን በሥርዓት ኮትኩቶ የማሳደግ ችግር በጥ ሞና መመልከት፣ የነገዋ ቤተ ክርስቲያን እጣ ፈንታ ምን እንደሚ ሆን ለማወቅ ነቢይነት አስፈላጊ አይደለም። አሁን አመራሩ የእኔ ነው ብሎ፣ የካህናትን የማስሪያ ሕግ ሲያረቅቅ የሚውለው ምእ መን ቆም ብሎ የሚሠራውን ማየት ይኖርበታል፤ አሳዛኙ ሁኔታ የቤተ ክርስቲያንን አመራር የያዙ ምእመናን ልጆች ቤተ ክርስቲ ያንን ብቅ ብለው ማየት የማይችሉና የማይፈልጉ እንዳሉ፣ እንሰ ማለን። ቤተ ክርስቲያንን ማስተዳደር አለብኝ ማለት ለዚህ ከሆነ ቆም ብሎ ማሰብን ይጠይቃል። በካህናትና በጳጳሳት መካከል እየገባ የሚያምሰው ሁሉ፣ ለዚህ ዓይነት መርሕ እርዳታ ቢያደ ርግ፣ ይልቅ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ምን ያህል በጠቀመ ነበር።

ከላይ እንደ ተባለው፣ ስደት የምንለው፣ ያልተወለድንበት ሥፍራ በመሆኑ ነው። አሁን የምንኖርበትን ሁኔታ ስደት ነው ማለት ግን ይከብዳል። ምክንያቱም ከዚህ መኖር ፈልገን ነው የመጣነው፤ እንዲያ ከሆነ ደግሞ ለቀሪው ትውልድ ቁም ነገር ጥለን ማለፍ ይጠበቃል ፤ ስለዚህ *"ስደትን ቋሚ አድርጎ በአንድነት መኖር"* የሚለው መርሕ፣ ከመሰብሰብ ያለፈ ፋይዳ ሊኖረው ይገባል። ማለትም ለዛሬ አሥር ዓመት፥ ለመቶ ዓመት፥ ለመቶ ኀምሳ ዓመት፣ ማሰብን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ያለንበትን ትውልድ የመተካት ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት እንሥራ። ይህንን ለማድረግም ቀጣዩን እናንብብ።

## 1.3. <u>በስደት ሆኖ ለአንድነት መሥራት፤</u>

ይህ ማለት፣ እናት ቤተ ክርስቲያን አገር ቤት መኖርዋን በዋና ቤተ ክርስቲያንነት ተቀብሎ፥ በውጭ ያለውን እንደ ቅርንጫፍ አድርጎ፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ለማስጠበቅ መሥራት ማለት ነው። ከሰው አገር የምንኖረው ተሰደን ሲሆን፣ የተሰደድነውም ተገፍተን ነው። ይህንን መርሕ እንደ መመሪያ አድርጎ መንቀሳቀስ ሲቻል፣ ታዲያ ከየት እንጀምር? የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት አለበት። ከዚህ ጥያቄ ስንነሣ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በሃይማኖታችን ጣልቃ በመግባቱ፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በመጣሱ ምክንያት፥ ፓትርያርኩ በስደት ላይ ናቸው። የፓትርያርኩ መሰደድ ቤተ ክርስቲያኒቱን እንድትሰደድ አድርጓል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግሥት የሃይማኖት ነጻነታችንን እስኪ መልስ፤ ቀኖናችንንም እስኪያከብር ድረስ፣ ቤተ ክርስቲያን በስደት



ሁና፣ ትሠራለች ነው መልሱ። በስደት የምትሰጠው ሐዋርያዊ አገ ልግሎት እንደ ተጠበቀ ሁኖ፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የሚያከ ብር፣ የዜጎችን መብት የሚያከብር ፍትሐዊ መንግሥት እንዲ መጣ፣ ብሔራዊ እርቅ እንዲመቻች፤ ሥራ ያስፈልጋል። ይህን መሠረተ ሐሳብ እንደ ዋና ግብ ማድረግ ከተቻለ፣ የምንሠራው ሥራ በራእይ ደረጃ መቀመጥ አለበት።

### ሀ/. <u>ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ማስጠበቅ ይቻላል?</u>

ቀኖና መጣሱ ለእምነቱ አለመጠበቅ አደገኛ ከመሆኑም በላይ፣ ይኸው ቀኖና መጣሱ ቤተ ክርስቲያንን አሳድዷል፤ ሕዝበ ክርስቲያኑን ከፋፍሏል። ከፍ ብሎ በቦታው እንደ ተገለጠው በዚህ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በሦስት የተከፈለ ቡድን የሚንቀሳቀስባት ሁናለች። ይህም ከፍቅር ይልቅ ጠብን፣ እያስፋፋ ሄዷል፣ ቤተ ክርስቲያን እንደ አሁኑ ጊዜ ከባድ ችግር ገጥሟት አያውቅም። ይህንን ሐሳብ በምናነብበት ጊዜ ጠቅላላ የኢትዮጵያን ያለፈ ታሪክ የምናይበት ይሆናል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ከሚባሉት አብያተ ክርስቲያናት፣ አንዷ እንደ መሆኗ መጠን፤ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የምታከብር ቤተ ክርስቲያን ናት።

ይህ ቀኖና አክባሪነቷ ነው በእስክንድርያ ሥር ለአንድ ሺህ ስድት መቶ ዓመት እንድትኖር ያደረጋት። የራስ መቻሉም ሁኔታ የተከናወነው ቀኖናው በሚፈቅደው መሠርት ነው። ይህ ነው አሁንም መጠበቅ ያለበት። ይህ ሥራ የዕለት አገልግሎት ከማድረግና ክብረ በዓል ከማክበርና ሕንጻ ከመገንባት በላይ እንድናስብ የሚያደርግ የእምነት ህልውና ጉዳይ ነው። እምነት

አስጠባቂው ከሌለ፣ እምነቱ ሊኖረ አይችልም። እምነት
አስጠባቂው ማለትም ትውፊታዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ነው።

ቤተ ክርስቲያን እንድትጠነክር ብቻ ሳይሆን እንድትኖር ካስፈለገ፣
ይህ ሕግ ተጠብቆ መኖር ይኖርበታል፤ ይህን ሕግ ጥሶ ቤተ
ክርስቲያንን አስጠብቃለሁና አገለግላለሁ ማለት ዘበት ነው።
ሥርዓተ ቅዳሴ በመባል የሚታወቀው የቅዳሴያችን መግቢያ ይህን
እውነት እንዲህ በማለት ያረጋገጣል፤

*"ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ኪዳንና
ሲኖዶስ ዲድስቅልያና የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት እስከ መጨረ
ሻው ያልተማረ ወደ ሕይወት መንገድ የሚያደርሱ እውነተኞች
የሆኑ ሕጎችን ሁሉ ያልተማረና ያላወቀ ቢሆን ለአገልግሎት ሥራ
ወደ ቤተ ክርስቲያን አይግባ። ምን አለብኝ በማለትና በመድፈር
ቢገባም ከመዐርጉ ይለይ፥ ከቤተ ክርስቲያን ይሰደድ፤ በመንፍስ
ቅዱስ ትምህርት ፈጽሞ ያስተዋለ ቢሆን የአብጥሊስን ትእዛዝ
ዐውቆ ለማገልገል ይግባ"።* [700]

ይህ ቃል ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ቀኖናን በማክበር ዋና መሆንዋን
የሚያመልከት ነው። ይህ ቃል ብቻ ሳይሆን በዛ ያሉ የቀኖና
መጻሕፍትን፣ ሰነዶችን፤ በቋንቋዋ የያዘች ቤተ ክርስቲያን ናት።
ይህ ሊታበል የማይችል ሐቅ ነው። እንዲህ ከሆነ፣ ተጠያቂ የሆነ
ሁሉ አጥብቆ ሊሠራ ይገባል፤ ይህ ነው ሃይማኖቱን

[700] *መጽሐፈ ቅዳሴ*



የሚያስጠብቀው። ይህን ካላደረገ ግን፣ ሲኖዶስ የሚለው ስያሜ
ብቻውን ምን ይጠቅማል። ቅዱስ ሲኖዶስ በሚለው ስያሜ
ሊጠራበት የሚችለው፣ የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት
ሲያስጠብቅ ብቻ ነው። ያ ካልሆነ፣ እንደ ተቋም መታመኑ
ያጠራጥራል። ስለዚህ በስደት ሁኖ ለአንድነት መሥራት የሚለው
መርሕ ቤተ ክርስቲያንን ብቻ ሳይሆን የዜጎችንም ነጻነት የሚያጠ
ቃልል ስለሆነ፣ ይህንን ስናስብ ወደ ቀጣዩ ነጥብ ይወስደናል።

## ለ/. ብሔራዊ እርቅና ሰላም፤

ይህ ሂደት በኃላፊነት መምራት ፖለቲከኞች ኀብረት የሚሉት የፖ
ለቲካ ስምምነት ብቻውን፣ ለኢትዮጵያ ጥቅም አይሰጥም። ይህ
ዓይነት ስምምነት፣ ከአሁን ቀደም ተሞክሮ ያልተሳካ ውጤት
አምጥቶ አገርንና ቤተ ክርስቲያንን ከአደጋ ያደረሰ ውጤት ነው።
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፣ ከስደት ተመልሶ ሕጋዊ መስ
ተዳድር ሲያቋቁም፣ ሦስቱን ቡድን በይቅርታና በእርቅ፣ ችግሩን
በማቃለል ፈንታ በአዋጅ አንድ ሁኑ የሚለው መንግሥታዊ ትእ
ዛዝ ስደተኛን፥ ባንዳን፥ አርበኛን፥ አንድ ከማድረግ ይልቅ፣ ውስ
ጣዊ በቀልን እያሳደገ ሂዶ፣ የቤተ ክርስቲያንና የአገርን አንድነት
የሚንድ ችግርን ፈጥሮ ነው ያለፈው። አሁንም መንፈሳዊ የይቅር
ታና የእርቅ ሂደት ካልተከናወነ፣ የሥርዓት ለውጥ ብቻውን ቤተ
ክርስቲያኒቱንም ሆነ አገሪቱን ወደሚፈለገው የሰላምና የአንድነት
ጉዞ ማድረስ አይችልም።

በአሁኑ ጊዜ የሚጻፉ መጻሕፍት፣ የሚያሳዩት ይህን ያለ ይቅርታና
እርቅ የተደረገ ስምምነት ውጤትን ነው። ለምሳሌ የቅንጅትን ስም
ምንነት ብንመለከት ውስጣዊ በቀልና ፉክክር እንደ ነበር

በዶክተር ብርሃኑ ነጋ መጽሐፍ መመለከት ይቻላል፤ ያም በተለይ በአቶ ልደቱና በእንጅኔር ኃይሉ መካከል ያለው የውስጥ አለመግባባት ከምርጫ በኋላ ለመጣው ልዩነት ዋና ምክንያት ነበር።[701] የፍትሕ ጋዜጣ አዘጋጅ ጋዜጠኛ ተመስገን፣ በፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ የአሥራ ሁለት ዓመት መታሰቢያ በዓል ላይ ተገኝቶ የታዘበውን መከፋፈል የገለጠበት ቋንቋ አእምሮን ይሰቀጥጣል።

*"የፕሮፌሰር አስራት የሙት ዓመት መታሰቢያ ከሚባል፣ የመኢድ የሙት ዓመት መታሰቢያ ቢባል ይቀላል ይላል"።* [702] ቅንጅትን በተመለከተ ፓርቲውን ከደዋል የተባሉት አቶ ልደቱም፣ ችግሩ ከቅንጅት ድክመት እንጂ፣ ከእኔ አይደለም ሲሉ፣ *"የአረም እርሻ"* የሚል መጽሐፍ ጽፈው አስነብበዋል። ይህን ሐሳባቸውንም ሰፊ ቦታ ሰጥተውታል፤[703] ዳንኤል ገዛኸኝ በተባለ ጋዜጠኛ፣ *'ሲዋን'* በሚል ርእስ የተዘጋጀ መጽሐፍ ላይ፣ በሙሉ ማለት ይቻላል በኅብረተሰባችን ያለውን የበቀል ጥርቅም በሚያሳዝን ሁኔታ ያስነ ብበናል።[704] ለምሳሌ ያህል እነዚህን፣ ጥቂቶቹን ገለጽን እንጂ፣ በየትኛውም በእኛ ትውልድ ያለው የበቀል ጥርቅም እንዲህ በቀ ላሉ ተገልጦ የሚያልቅ አይደለም።

*701 ብርሃኑ ነጋ ዶክተር፣ የነጻነት ጎህ ሲቀድ፣ የምርጫን ሂደትና የመንግሥትን ሥርዓት በገለጡበት ክፍል ከገጽ 289-352*

*702 ጋዜጠኛ ተመስገን፣ የመለስ አምልኮ ገጽ*

*703 ልደቱ አያሌው፣ የአረም እርሻ ከገጽ 73 -110.*

*704 ሲዋን ዳንኤል ገዛኸኝ ገጽ 132-160*



በዚህ በቀል ውስጥ እንዳሉ፣ አንድነት መመሥረት ማለት ፈንጅ በተጠመደበት ድልድይ ላይ እያወቁ መኪና እንደ መንዳት የሚቈጠር ነው። ለዚህ መድኃኒቱ ቤተ ክርስቲያን ይህን እድል ተጠቅማ በተቃዋሚው ወገን በኩል የሚከናወን የእርቅና የሰላም ሂደት ማድረግ ያስፈልጋታል። ምክንያቱም የስደቱ መነሻ የፖለቲካ ነጻነት በሌለበት አገር ላይ የሃይማኖትም ነጻነት ስለሌለ ነው። ለስደት የበቃነው።

ይህ መጽሐፍ እየተጻፈ እያለ በኢትዮጵያ እስላሞች ላይ የሚካሄደውን የሃይማኖት ተጽዕኖ ስንመለከት ነበር። ይህ ተጽዕኖ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከዛሬ ሃያ ሁለት ዓመት ጀምሮ በመካሄድ ላይ ነው። በዚያ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስደት፣ እንደ ግለሰቦች ጉዳይ ተድረጎ ነበር የተወሰደው፤ አሁንም ገዳማትን መድፈር፣ አብያተ ክርስቲያናትን ማቃጠል፣ እንደ ቀጠለ ነው። ለዚህ ጥፋትም የአዲስ አበባው ቤተ ክህነት ተባባሪ ሁኖ እየሠራ ነው። ለዚህ መሠረቱ በኢትዮጵያ የሕዝብንና የሃይማኖትን ነጻነት የሚያከብር መንግሥት እስኪቋቋም ድረስ ቤተ ክርስቲያን ጥረቷን ትቀጥላለች። ከምትሠራው ሥራም አንዱ፣ ይህንን የሰላምና የእርቅ ሂደት ማካሄድ ነው። ይህም ዋናው ሥራ አነሣሽና ዓላማ መር አቋም መሆን አለበት።

## ሐ/. **የመሪነት ብቃት፤**

መሪነት ስንል ግትር ከአላዋቂ ግለሰቦች ጋር ወግኖ ግትር አቅዋ ምን ማሳየት ማለት አይደለም። ከነገረ ሠሪዎች ጋር መንጎድም አይደለም። መሪነት ለራእይና ለዓላማ መቆምን እየተመለከቱ፣

ለነገ የሕይወት ጎዳና መጥረግ ነው። መሪነት ማለት ሌሎችን የመጉኛ መሣሪያ አይደለም። ሌሎችን የመርጃ ጥበብ ነው። መሪነት አንድን የራስ ብቸኛ ሐሳብና አጀንዳ የምናስፈጽምበት መሣሪያ ሳይሆን፣ አንድን ችግር የምንፈታበት፣ ቁልፍ ነው።

በአገራችን ጥሩ አስተዳዳሪ ማለት፣ አንድን ጉዳይ አጭበርብሮ፣ ወይም አወሳስቦ በተንኮሉ ተፈጻሚነት ያላደረሰ እንደ ሆነ ነው። በዚህ ባለንበት አገር ያሉ አገልጋዮች እንኳ ጎበዝ ሲባሉ፣ የምንመለከታቸው፤ ወይ በግትር ሐሳባቸው ሰውን ያስመረሩ ወይ በተነኮላቸው ሰውን ያሳደዱ ናቸው። በዘመናዊ የመሪነት ሚዛን ግን ይህ ማጥፋት እንጂ መምራት አይደለም። እንዲህ ከሆነ፣ መሪነት ምንድን ነው? መሪነት የተለያዩ መለያ ባሕርያት ሲኖሩት የሚከተሉት ግን ጥቂቶቹ ናቸው።

ሀ/. <u>መሪነት የራእይ ጥበብ ነው፤</u>

መሪነት ወደ ፊት የዓመት፥ የሁለትና የሦስት ምዕት ዓመታት እቅድን በማውጣት፣ ለተከታዩ ትውልድ የሚተርፍ ራእይ መንደፍ ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሙሴ፣ በተለይም የኢያሱ የመሪነት ጥበብ፣ አሁን ላለነው ትልቅ መመሪያችን ነው፤ በምዕራፍ አንድ የተጠቀሰውን የእግዚአብሔርን ቃል በማመን፣ ሕዝቡን እስከሚያደርስበት ድረስ መራ። በእያንዳንዱ ሥራ ሂደት የሚያደርጋትን በትጋት ያደርግ ነበር። ሕዝቡን ሲመራ የእርሱን ሐሳብ ሳይሆን፣ የእርሱን ዓላማ እንዲከተል ያደርግ ነበር፤ የእርሱ



ዓላማ ማለት የእግዚአብሔር ሐሳብ ማለት ነበር።[705] በዚህ ዙሪያ ላይ የዘመኑ ጸሐፍት ይስማማሉ።[706]

መሪነት፣ ሌሎችን መደገፍ ስለ ሆነ ዕውቀትን፣ ጉልበትን መለኪያ አያደርግም፤ መሪነት ትሕትናን የተላበሰ መንፈሳዊ ሰውነትን ይጠይቃል። ቀደም ሲል የነበረው የመሪነት፣ ጥበብ ከበላይ ሁኖ ወደ ታች የሚል ነበር፤ አሁን ግን የመሪነት እውነተኛ ብቃት የሚመዘነው፣ መሪው ከሚመራው ሠራተኛና ሕዝብ ጋር እንዴት ይሠራል? በሚለው ነው። በተለይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመሪነት ብቃታቸውን ማስመስከር ያለባቸው ለሚመሩት ሕዝብ በሚያሳዩት ትሕትናና ፍቅር ነው።[707]

የቤተ ክርስቲያን መሪነት፤ መንፈሳዊነት፥ አባታዊ ፍቅርና ርኅራኄ ካልተጨመረበት ከሦስተኛው ዓለም አምባ ገነኖች በምን ይለያል? ቤተ ክርስቲያን ይህን በስደት የተንገላታና ብዙ ብሶት ያለበትን ሕዝብ፣ ከእግዚአብሔር በተሰጣት መንፈሳዊ ፍቅር ማስተናገድ ይኖርባታል። ለዚህም፣ የክርስቶስ የመሪነት ምሳሌ ትልቁ መመሪያ ነው። ለተናቁት ጊዜ ሰጥቶ ያናግር ነበር።[708] ሰው የሌላቸውን ልትድን ትወዳለህን? በማለት ኃይልና ፈውስ ይሰጥ ነበር። ደቀ መዛሙርቱንም በማሠልጠን በየጊዜው ያበረታቸው ነበር።[709] ቤተ

---

- ኢያሱ 3፡ 1-8 ፤ እንዲሁም 4 ፥ 4-14 መመልከት ይቻላል። በመጨረሻም ምዕራፍ 24፡ 15-24
- Andy Stanley Visioneering Gods Blueprint for Developing and Maintaining Vision.pp. 17—28.

[707] Leonard Doohan ,Spiritual Leadership .pp. 35-50

[708] Ibid

[709] Mary Kate Morse, Making Room for Leader ship, powr, space and influence. Pp. 51-58.

ክርስቲያንም ከጌታዋ በተማረችው የመሪነት ጥበብ ምእመናንን በትሕትና፥ በፍቅር፥ በትዕግሥት፥ መምራት ይገባታል።

ሸካራ አመለካከት በመረዘው ተክለ ሰውነት እየተመሩ፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስጠላ ነገር መናገር ግን፣ ወይ ዓላማን አያሳካ፥ ወይ ራስን አያስከብር፤ ትዝብት ብቻ ጥሎ ይሄዳል። ስለዚህም የመሪነትን ብቃት ቤተ ክርስቲያን ለኅብረተሰቡ ልታሳየው የሚያስፈልጋት ትልቁ ሥራዋ ኃለፊነቷ ነው።

ለ/. <u>መሪነት የችግሮች መንሥኤ ማግኛ ጥበብ ነው፤</u>

መሪነት ሁሉን በእኩልነት በማዳመጥ የችግሩን /የበሽታውን/ መን ሥኤ የማግኛ ጥበብ ነው። የመሪነት ጥበብ የሚለካው ችግሮችን የሚያዩበት ጥበብ ሲሆን ብቻ ነው። [710] የሰውን ግንዛቤ፣ የጊዜና የቦታን ሁኔታ፣ ማመዛዘንና የሌሎችን ሐሳብ በመቀበል ትክክለኛ ውሳኔን የመወሰን ጥበብ ነው። በመሪዎች አለማወቅ ወይም ዐውቀው የጠፉ ጥፋት ለማስተካከል ዋጋ ያስከፍላል። ብዙ ጊዜም በጠፋው ጥፋት የተነሣ ነገሮችን መልሶ እንደ ነበር ማድረግ አይቻልም። ይህም የጊዜያዊ /የታይታ/ ሥራ እንቅፋት ብቻ ሳይሆን ታማኝነትንም አያስገኝም።

መሪነት፣ ለመስማት በመፍጠን፥ ለመናገር በመዘግየት፥ ሚዘናዊ ብቃትን በማዳበር የሚሠራ ነው። ይህን ተፈላጊ ባሕርይ ቻል ብሎ የሁሉን እኔ ልፍጀው መርሕ ለመሪነት አያበቃም። መሪነት የብዙዎችን ዕውቀት፣ ጉልበትና ገንዘብ የሚጠይቅ ጥበብ ነው።

---

[710] Ronald Heietz The Practice of Adaptive Leadership. Pp. 50-54.



ስለ ሆነም ቤተ ክርስቲያን በስደት ሁና ለአንድነት የምትሠራው ሥራ ለመሪነት የሚሄዱ ሰዎችን ማሠልጠን፣ የሚካሄዱ ስብሰባዎችን አጀንዳ ከዓላማ ጋር ማዛመድ፣ የሚሠሩ ሥራዎችን ቅደም ተከተል በማውጣት፣ ለቀዳሚው ትኩረት መስጠት ይገባል።ነገ አንድ ነገር ቢሆን፣ ያለኝ መመሪያ፣ የምሠራው ሥራ ይህ ነው፣ ማለት ይኖርባታል።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ዓላማ መርና ሥራ አነሣሽ ነጥቦችን ይዞ የተበተነውን ወደ አንድ አቅጣጫ መሰብሰብ ያስፈልጋል። በቁጣ ለውግዘት መፍጠን የአምባ ገነንነት መለኪያ እንጂ፣ የብልህ መሪነት ምልክት አይደለም። ለዚህማ ወያኔ በቂያችን ነው። እኔ ብቻ ዐውቅላችኋለሁ በማለት እውነቱን የሚነግረውን ሁሉ እየዘለፈ፣ ሲፈልግ የሚገድለውን፣ ሲፈልግ የሚያሥረውን የዜጋ ስቃይ የምንመለከተው የአምባገነኖች ሂደት ውጤት ነው። ለነገሩማ አሜሪካን አገር ላይ አገልጋይ ካህናትን ከማሳሰር በላይ ምን ዓይነት አምባ ገነንነት ይመጣል?

## 2. <u>ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች፤</u>

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስንመለከት፣ ቤተ ክርስቲያን ራሷን የገለ ጠችው፣ ማንነቷንም ይዛ የቀጠለችው በሦስት ጠንካራ ምሰሶዎች ላይ ተደግፋና ተጠብቃ ነው። እነዚህም፦

- 2.1. **ቅዱሳት መጻሕፍት፣**
- 2.2. **ቀኖና ቤተ ክርስቲያን፣**
- 2.3. **ቅዱስ ሲኖዶስ፣ ናቸው።**

እነዚህ ሦስቱ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ላይ ከፍ አድርገው፣ ደግፈው የያዟት ምሰሶዎች ናቸው፤ ከእነዚህ አንዱ ከጎደለ፥ ቤተ ክርስቲያን ሚዛናዊ ሁና ጸንቶ መቆም አይቻላትም። በዚህ መጽሐፍ ለማስረ ዳት የተሞከረው እነዚህን ሦስት ምሰሶዎች ካህናትም፣ ምእመና ንም በሥርዓትና በአግባቡ መጠቀምና አለመጠቀማችንን ማሳየት ነው።

2.1. <u>ቅዱሳት መጻሕፍት፤</u>

አሁን ባለንበት ደረጃ የምንቀበላቸው ሰማንያ አንዱ ቅዱሳት መጻ ሕፍት የተባሉትን በቍጥር ደረጃ እንቀበል እንጂ፣ የተለያየ ቍጥር ስላለ ብዙ አከራካሪ ነገሮች ይታያሉ፣ ሁኖም ግን መጻሕፍትን ቈጥረን መያዛችን፣ ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዊ ትውፊት የተ ቀበልነው መሆኑን ተመልክተናል። ይህም ክርስቶስ ለቤተ ክርስ ቲያን የሰጣት መሣሪያዋ ነው። ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውና እንድታስተምር የታዘዘችው በብሉያትና በሐዲሳት መጻሕፍት፣ የተገለጠውን ክርስቶስን ነው። በዚህ መጽሐፍ መጠነኛ ማብራ ሪያ የተሰጠው፣ ይህ መርሐ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን እንዴት በሥራ ላይ እንደ ዋለና ቤተ ክርስቲያንን እንዴት አድርጎ እንደ ጠበቀ ነው።

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን፣ አባቶች ይህንን ሥራ ሲሠሩ ብዙ የሕይወት ዋጋ ከፍለዋል። የቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሆነው፣ ቅዱስ መጽሐፍ አሁን በእጃችን ሊገባ የቻለው፣ እነርሱ በከፈሉት ዋጋ ነው። ቤተ ክርስቲያን ሕያው ሁና የምትኖረውና የኖረችው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው። በዚህ መጽሐፍ በዋናነት የተብራራው



ግን ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷን ሲያስጠብቅ የኖረው ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ነው።

2.2. <u>ቀኖና ቤተ ክርስቲያን፤</u>

ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የምንለው፣ በቤተ ክርስቲያንናችን ትልቅ ቦታ የተሰጠው፣ ነገር ግን በአሁኑ ትውልድ ያልታየ ትምህርት ነው። ትውልዱ አየሁት የሚለው በአሪት ስለ ተደነገጉ ሕጎች እንጂ፥ ቤተ ክርስቲያንን ቤተ ክርስቲያን ያሰኛትን ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን አይደለም። ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ግን፣ ቤተ ክርስቲያንን በራስዋ አቅጣጫ አስያዥ፣ በተለይም ከሕግ ውጭ የሚጓዙ፥ ቤተ ክርስቲያንን ሥጋዊ መጠቀሚያ ለማድረግ የሚጥሩ፥ በየጊዜው የሚነሡ ሥርዓት አልበኞችን፥ ሥርዓት በማስያዝ የሚቈጣጠር ሕግ ነው።

ለዚህ ይመስላል፥ እውነት የሆነውን ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን እየጠሉና ሌላ ስምም እየሰጡ፥ በቀላሉ ሕዝብ የሚደናገርባቸውን ሰዋዊ ሕጎችን እውነተኛ አስመስለው የሚያቀርቡት። ይህ ጉዳይ እንደ ትልቅ ዝብዱ፣ እሚቆጠረበት ጊዜ ስለ ሆነ፣ ይህ መጽሐፍ በዚያ በኩል ያለውን ክፍተት ቀላል በማይባል መልኩ ሊያጠበው ይችላል።

የኢትዮጵያ ኦርቶደክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ ከጥንት ጀምሮ ተያይዘው የመጡ የሕግና የሥርዓት መጻሕፍት አሏት። እነዚህም ፣ መጽሐፈ ሲኖዶስ ዘ፲ወ፪ (አስራ ሁለቱ) ሐዋርያት የተባለ መጽ ሐፍ፣ ትምህርተ ዲድስቅልያ ዘአበው የተባለ መጽሐፍ፣ የጥንት ቀኖና ስብስብ የሆነው ፍትሐ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ ናቸው።

ይህ ሁሉ ተሰባስቦ አንድ ወጥ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መመሪያ መውጣት ይኖርበታል። ትውልዱ ሊያውቀውና ሊጠብ ቀው የሚገባ ትምህርት ነው። ለሰው በሚገባ ቋንቋ ተተርጕሞ፣ ቢዘጋጅ ኑሮ፣ ዛሬ በጉንጭ አልፋ ክርክር ጊዜ ከምናጠፋ ይልቅ እውነት በሆነው ነገር ላይ ተወያይቶ መፍትሔ ማግኘት ይቻል ነበር።

አሁን ባለንበት ደረጃ የችግራችን መነሻ በሆነው ጉዳይ እንኳ መተ ማመን አልቻልንም። በእርግጠኝነት ለመናገር፣ ሦስት ሰዎች ቢሰ በ ሰቡና የቤተ ክርስያን ችግር የሆነውን ዋና ነገር እንዲያወጡ ቢጠየቁ፣ በመፍትሔው ሳይሆን በችግሩ እንኳ መስማማት ያቅታ ቸዋል። ይህ መጽሐፍ ቢያንስ ለዚህ ችግር፣ ጠቋሚ እንዲሆን ስለ ተዘጋጀ፤ የችግራችንን አቅጣጫ እንኳ በዚህ መንገድ ማየት ይቻ ላል።

በየትኛውም የሞያ መስክ ፣ ሕግና ሥርዓትን የሚያስጠብቅ አካል ወሳኝነት አለው፤ ለዚያ አካልም መሥሪያና አሠሪ ደንብ ያስፈል ጋል። ያ ነው እንግዲህ ለጤናማ እድገት የሚያበቃ፤ ቤተ ክርስ ቲያንም በረጅሙ ታሪኳ፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተባለው ሕግና ሥርዓቷ ከሐዋርያት ጀምሮ እያደገ የመጣ ሕግና ሥርዓት ነው። በዚህ ሕግ ነው ትምህርቷና አንድነቷ፣ ተጠብቆላት መንፈሳዊና ማኅበራዊ ጉዳዮቿን ስታከናውን የኖረችው። ለዚህም የተካሄዱት ጉባኤዎቿ ማስረጃዎች ናቸው። አሁን የያዝነው እምነት የእነዚያ ጉባኤያት ውጤት ነው። በቤተ ክርስቲያናችን ከተቀበልናቸው ቁም ነገሮች አንዱ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ነውና ልንጠቀመበት ይገባል።



## 2.3. <u>ቅዱስ ሲኖዶስ፤</u>

በቀኖና መጻሕፍት ሕግ ከለላና ግልጽ መመሪያ የሚገኘው ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አመራሯን በትክክል እንድታስተዳድር፣ የሚያደረጋትን መብት የሰጣት፣ ቀኖና ነው። በዚሁ ቀኖና ሕግ የቤተ ክርስቲያን የሥልጣን ምጭ የሆነው ሲኖዶሳዊ ምልዓተ ጉባኤ፣ ምን ዓይነት ሰው አባል እንደሚሆን፤ የሲኖዶሳዊ ጉባኤ ምሉዕ ነው የሚባለው ወይም የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ሊወክል የሚችለው ምን ያህል ቍጥር እንደ ሆነ፣ አንድ የሲኖዶስ አባል ለሲኖዶስ አባልነት የሚያበቃው መመዘኛ ምን እንደ ሆነ፣ በማን እንደሚሾም፣ የሚገልጽ ሲሆን፤ ሥልጣን የሚያሳጡና ለሥልጣን ከለላ የሚሆነው፣ የሥልጣን የጊዜ ገደ ብም እስከ ሞት የሚለው የሥልጣን እስጠባቂ ሕግና የሚሰጠው መብትም በዚሁ ቀኖና ብለን በምንጠራው ሕግ ላይ ይገኛል።

ይኸው ቅዱስ ሲኖዶስ በመባል የሚታወቀው፣ የቤተ ክርስቲያን የሥልጣን ምንጭ፣ ለቤተ ክርስቲያን አንድንት፣ ለትምህረቷ መጠ በቅና ለጥንካሬዋ መሠረት ሁኗት፥ ሁለት ሽህ ዓመታትን አሳልፋ፤ እኛ እስካለንበት ክፍለ ዘመን ደርሳለች፤ በመሆኑም በስደት ያለው ሲኖዶስ ሕጋዊነት የሚረጋግጠው፣ የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ሕገ ወጥነት የሚጋለጠው ከዚህ ስንነሣ ነው። ቀኖናው እያንዳንዱን የቤተ ክርስቲያን የሥልጣን ተዋረድ፣ ከዲቁና እስከ ፐትርክና በደርጃ ያስቀመጠው፣ ይህን የቤተ ክርስቲያን ሕግ እንዳሻው ማድረግ የማይችል በመሆኑ ነው፣

የአሁኑ ትውልድ፣ ይህ ሕግ እንዳለ ይናገራል፤ የዲቁና ሥልጣን የቅስና መብት እንዲጠበቅ፣ የቤተ መቅደስ ሥርዓት እንዲጠበቅ

ያስተምራል። ከዛም አልፎ ስሕተት ተፈጸመ በማለት ብዙዎችን ይወቅሳል። ትልቁ አሳዛኝ ጉዳይ ግን የቤተ ክርስቲያን የሥልጣን ምንጭ የሆነውን ሲኖዶሱንና የጵጵስናውን ሥልጣን ሲክድና አል ቀበልም በማለት፣ ቤተ ክርስቲያናችንን እንደ ካደና በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በውግዘት የተላለፈውን ውሳኔም በኃላፊነት እንደሚ ወስድ የተገነዘበ አይመስልም ወይም መስማት አይፈልግም፤ አሁ ንም ቤተ ክርስቲያን ውበቷንና ማንነቷን ይዛ እንድትቀጥል ካስፈለገ፣ ሕገ ወጥነት ይወገድ፤ ሕጋዊነት ይከበር፤ በሕጋዊነት መቀለድም ይቁም፤ እንላለን። እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ምሰሶዎች ሊኖሩ የሚችሉት ቀኖና ሲኖር፣ ሕጉ ሲከበር ነውና።

**እነሣሥቶ ላስጀመረን፥ አስጀምሮም ላስፈጸመን፥**
**ሁሉን ቻይ ለሆነው አምላክ፣**
**ምስጋና ይሁን፤**
**አሜን።**



## <u>የአማረኛና ግዕዝ እንዲሁም የመጽሔት ዋቢ መረጃዎች፤</u>


-ለይኩን ብርሃኑ ዶክተር፣ <u>ለምንት አንገለጉ አሕዛብ</u>፤ 1997 ፌርፋክስ ቨርጅኒያ ዩናትድ ስቴት ኦፍ አሜሪካ።

-ሉሌ መላኩ፣ <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u> ለሦስተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የታተመ፤ አኩስም ማቴማ ቤት፣ 1997 አዲአስ አበባ ኢትዮጵያ።

-ሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ፣ <u>ትምህርተ ሃይማኖት ክርስቲያናዊ ሕይወት፤</u> አሳታሚ ማህበረ ቅዱሳን፣ 1996 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ።

-ልደቱ አያሌው፣ <u>የአረም እርሻ</u>፤ 1998 አዲስ አበባ ኢትዮጳያ

-<u>መጽሐፈ ቅዳሴ</u>፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፋድና ትእዛዝ፣ ትንሣኤ ማሰተማያ ደርጅት 1984 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ።

-<u>ማኅበረ ቤተ ክርስቲያን</u>፣ ለምዕራብ ሀገሮች ሀገረ ስብከት አስተዳደር የወጣ ደምብ ሚያዝያ 2 / 1992 በተጻፈ መሸኛ የተላከ መመሪያና መዋቅር።

-<u>ሥርዓተ ግጽው፣</u> የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቀኖና መጻሕፍት አንድ ክፍል ነው።

-ያረጋል አበጋዝ፣ <u>ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ</u>፣ /ትርጉም/።

-ቤተ ክህነት፣ <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዐት ራስን የመቻል ታሪክ</u>፣ ክፍል አንድና ሁለት።

-ብርሃኑ ነጋ ዶክተር፣ <u>የነጻነት ጎህ ሲቀድ</u>፣ ከቃሊቲ እስር ቤት 1998።

-ተስፋዬ መኮንን፣ <u>ይድረስ ለባለታሪኩ፤</u> 1985 አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ማተሚያ ቤተ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ።

-ነጸብራቅ መጽሔት ልዩ እትም፣ ጥቅምት 2000
-አባ መልከ ጼዴቅ፡ሊቀ ጳጳስ፣ የቋዋሚ ምስክርነት፣ 1995 እንደ ኤ አቆጣጠር ዓለም ማተሚያ ቤተ አከላንድ ካሊፎርኒያ።
-አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ፣ ሕግን ጥሶ ሕጋዊ መሆን ይቻላልን? 2007 እንደ ኢሮፓ አቆጣጠር ኒዉ ዮርክ።
-የማይገለጥ የተከደነ የለም፣ ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለሕገ ወጡ የወያኔ ሲኖዶስ የተሰጠመልስ።
-አባ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ 1991 ፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ።
-አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ነጻነት ያማያውቅ ነጻ አውጭ።
-ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት፤ አርቲስቲክ ማተሚያቤት 1948 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
-ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም፣ ትግላችን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ትግል ታሪክ 2004 ፀሐይ አሳታሚ ድርጅት ሎስ አንጀለስ ካሊፎርኒያ።
-የብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት የበዓለ ሢመት፣ መጽሔት ልዩ እትም አንደኛ ዓመት።
-የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በዓለ ሢመት፣ አንደኛ ዓመት መጽሔት።
-የአባ ጳውሎስን አሿሿም የገለጠው ጦቢያ መጽሔት፣ ነሐሴ 1984 ቊጥር አምስት።
-የአብጥሊስ /ሥርዓተ ግፅው፣ የኢትዮጵያ ቀኖና መጻሕፍት።
-የድጋፍ ሰጭ ኮሚቴና የማኅበረ ተዋሕዶ አማካሪዎች ያወጡትን ደንብ ናሙና በዚሁ በዋቢ ዝርዝር ውስጥ ይመልከቱ።
-ዮሐንስ መሸሻ፣ የኢትዮጵያ አስተዳደር የፖለቲካዊ ሂደት፣ 1996 እኤአ ፊደል አሳታሚ ሎስ አንጀለስ ካሊፈረኒያ።
-ደበበ እሸቱ፣ የእመቴ ፈተና፣ ከምርጫ 97- ቃልቲ 2000 ሊንክ ግሎባል አሳታሚ ዋሽንግተን ደሲ።



-ዲበ ኩሉ ዘውዴ ዶክተር፣ ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖና! ብርሃንና ሰላም ማተሚያቤት 1986 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ።
-ዲበ ኩሉ ዘውዴ ዶክተር፣ 81 ቅዱሳት መጻሕፍትና ምንጮች! ቀኖናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን።1987 አዲስአበባ።
-ትምህረተ ዲዲስቅልያ ዘአበው፣ ሐዋርያት በግእዝና በእንግሊዘኛ በውጭ አግር የታተም አሁን በጉግል ለጥናት ተብሎ የተለቀቀ።
-ገሪማ ታፈረ፣ ጎንደሬ በጋሻው፣ 1940 በተስፋ ገብረ ሥላሴ ማጠሚያ ቤት አዲስ አበባ።
-ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል ሁለት፤ 1993 አዲስ አበባ።:
-ጋዜጠኛ ተመስገን፣ የመለስ አምልኮ፣ ዲስ አበባ።
-ጦማረ ጴጥሮስ ወመጽሐፈ ሲኖድ ዘአሠርቱ ወክሌቱ ሐዋርያት።
-ፍትሐ ነገሥት፤ ንባቡና ትርጓሜው፣ 1962 አድስ አበባ ኢትዮጵያ። ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

## BIBLIOGRAPHY

Athanasius, On the Incarnation. St Vladimir's Seminary Press, Crest Wood, New York 1996.
------. Letters.
Barnes, Timothy. Athanasius and Constantius: Theol ogy and Politics in the Constantinian Empire. Cambridge: Harvard University Press, 1993.
Beckwith, Roger. Elders in Every City: The Origin and Role of the Ordained Ministry. Carlisle England: Paternoster Press, 2002.
Behr, John. The Way to Nicaea. Crestwood: St. Vladi-

mir's Seminary Press, 2001.
Bogolepov, Aleksandr. Toward an American Orthodox Church, Crestwood: St. Vladimir's Seminary Press, 2001.
Brown, Harold. Heresies: Heresy and Orthodoxy in the History of the Church. Peabody: Hendrickson, 2007.
Bruce, F. The Canon of Scripture. Downers Grove, Ill: Inter-Varsity Press, 1988.
Campenhausen, Hans von. The Fathers of the Church. Peabody: Hendrickson Publishers, 1998.
Clément, Olivier. Conversations with Ecumenical Patria rch Bartholomew I. Crestwood: St. Vladimir's Seminary Press, 1997.
Clement,of Rome, The First Epistle, to the Corinthians Cyprian of Carthage, On the Church selected Letters:-The Epistle, to the Lapsed.
-On The Unity of the Catholic Church.
-Concerning the Baptism of Heretics.
Davis, Stephen. The Early Coptic Papacy: The Egyptian Church and its leadership in late Antiquity. Cairo New York: American University in Cairo Press, 2004.
Erickson, John. The Challenge of our Past: Studies in Orthodox Canon Law and Church History. Crestwood: St. Vladimir's Seminary Press, 1991.
Gaillardetz, Richard. By What Authority?: A primer on Scripture, the magisterium, and the sense of the faithful. Collegeville: Liturgical Press, 2003.
Gonzalez, Justo. The Story of Christianity. New York:



HarperCollins, 2010.
Hardy, Edward. Christology of the Later Fathers. Philadelphia, Westminster Press, 1977.
Hippolytus. On the Apostolic Tradition.
Huillier, Peter. The Church of the Ancient Councils: The Disciplinary Work of the First Four Ecumenical Councils. Crestwood: St. Vladimir's Seminary Press, 1996.
Ignatius The Apostolic Fathers Volume I, Epistle to the Philadelphians. Epistle to the Ephesians. Epistle to the Magnesians.
Irenaeus, Against Heresy.On the Apostolic Preaching. Councils. Crestwood: St. Vladimir's Seminary Press, 1996.
Jurgens, William. The Faith of the Early Fathers: A Source-Book of Theological and Historical Passages. Collegeville: Liturgical Press, 1970.
Justin Martyr, The First and Second Apologies
Kärkkäinen,Veli-Matti፣ Introduction to Ecclesiology: ecumenical, historical & global perspectives. Downers Grove: Inter Varsity Press, 2002.
Küng, Hans. Christianity: Essence, History and Future. New York: Continuum, 1999.
McGrath, Alister. Christian Theology, An Introduction. Chichester: Wiley-Blackwell, 2011.
McGuckin, John. The Westminster Handbook to Patristic Theology. Louisville: Westminster John Knox Press, 2004.
Meyendorff, John. Living Tradition: Orthodox Witness

in the Contemporary World. Crestwood: St. Vladimir's Seminary Press, 1978.

Meyendorff, John. Catholicity and the Church. Crest wood: St. Vladimir's Seminary Press, 983.Morse, MaryKate. Making Room for Leadership: Power, Space and Influence. Downers Grove: IVP Books, 2008.

Nersoyan, Tiran. Armenian Church Historical Studies: Matters of Doctrine and Administration. New York City: St. Vartan Press, 1996

Ozment, Steven. The Age of Reform (1250-1550): An Intellectual and Religious History of Late Medieval and Reformation New Haven: Yale University Press, 1980.

Patsavos, Lewis . Spiritual Dimensions of the Holy Canons. Brookline: Holy Cross Orthodox Press, 2003.

Percival, Schaff, Wace. The Seven Ecumenical Councils Of The Undivided Church: Their Canons And Dogmatic Decrees Together With The Canons Of All The Local Synods Which Have ... From The Writings Of The Greatest Scholars. Oxford: Benediction Classics, 2011.

Pospielovsky, Dimitry. The Orthodox Church in the History of Russia. Crestwood: St. Vladimir's Seminary Press, 1998.

Quasten, Johannes. Patrology. Westminster: Christian Classics, 1983.

Ramet, Pedro, Ed. Eastern Christianity and Politics in the Twentieth Century. Durham: Duke Univer sity Press, 1988.



Ratznger,Joseph Cardinal Called to Communion: Under standing the Church Today. San Francisco: Ignatius Press, 1996

Shelley, Bruce. Church History in Plain Language. Nashville: Thomas Nelson, 2008.

Stanley, Andy. Visioneering: Gods Blueprint for Developing and Maintaining Vision. Sisters: Multnomah Publishers, 2005.

Tarazi, Paul. The Old Testament: An Introduction. Crestwood: St. Vladimir's Seminary Press, 1991.

Turrettini, François. Institutes of Elenctic Theology,. Phillipsburg: P&R Pub, 1992.

Volf, Miroslav. After our Likeness: The Church as the Image of the Trinity,. Grand Rapids: Eerdmans, 1998.

Ware, Timothy. The Orthodox Church. New York: Penguin Books, 1993.

Webber, Meletios. Bread & Water, Wine & Oil: An Orthodox Christian Experience of God. Ben Lomond: Conciliar, 2007.

Wood, Susan. One Baptism: Ecumenical Dimensions of the Doctrine of Baptism. Collegeville: Liturgical Press, 2009.

Wright, N.T. Acts for Everyone. Louisville: Westminster John Knox Press, 2008. Jesus and the Victory of God. Minneapolis: Fortress Press, 1997.

Zizioulas, Jean. Eucharist, bishop, Church: The Unity of the Church in the Divine Eucharist and the Bishop During the First three centuries. Brookline: Holy Cross Orthodox Press, 2001.

Zizioulas, Jean. The One and the Many: Studies on God, Man, the Church, and the World Today. Western American Diocese: Sebastian Press, 20120.